አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3594 | ቅዳሜ መስከረም 30 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ኢትዮጵያ - በተምሳሌትነት ምዕራፍ

- ባለፉት ዓመታት በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተገኙ ውጤቶች የአፍሪካ ተምሳሌት የመሆን ውጥኖችን ማሳካት እንደሚቻል አመላካች ናቸው

**በመለሰ ተሰጋ**

"ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት፤ ስለዚህ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን" ይህንን ያሉት እ.ኤ.አ ከ2017 እስከ 2023 የኖቤል ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩት ቤሪት ሬይስ አንደርሰን ናቸው፡፡ አጋጣሚውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በፈረንጆቹ አቆጣጠር የ2019ኙን የኖቤል ሽልማት ባገኙበት ወቅት ነበር፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር መንግሥት ምሥረታ ላይ "ኢትዮጵያ፣ ውድቀቷን ሲመኙ ትነሳለች፤ ድክመቷን ሲናፍቁ ጠንክራ ትወጣለች፤ ተበተነች አለቀላት ብለው ሳይጨርሱ ተሰብስባ ትነሳለች...፤ የኢትዮጵያ ነገር ትንግርት ነው!" ማለታቸውም ዋቢ ምስክር ነው፡፡

በእርግጥም ኢትዮጵያ ድንቅ ነች፤ እንደ ዳሎል በፍፁም ትህትና ዝቅ ብላ ሁሉንም የምታከብር፣ ደግሞም እንደ ዳሽን ተራራ ከፍ ብላ በኩራት የጀግንነቷን እና የነፃነት ተሚጋችነቷን የሚመሰክሩ ታሪኮቿን የምትናገር ቅኔ የሆነች ሀገር ናት ኢትዮጵያ።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል


ፎቶ:- ከገጸ ድር
ባለፉት ጥቂት ዓመታት የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ከፍታ የሚያረጋግጡ ታላላቅ የልማት ድሎች ተመዝግበዋል

## ሀገራዊ ጥቅምን ያስቀደመ የፖለቲካ ባህል

6


ፎቶ- ከገፀ ድር
በመንግስት ምስረታው የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮችም ሹመት አግኝተዋል

## ትውልድ ተሻጋሪ ልማት

8


ፎቶ- ከፋይል
የፒያሳ የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

## የማይዳሰሱ ቅርሶች ህያውነት በአዲስ አበባ

11


ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባ በተለያዩ የአደባባይ በዓላት የደመቀች ከተማ ነች

# የመዲናዋ ቱሪዝም መስፈንጠሪያ ርካቦች

- መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ተጨባጭ ውጤት እያመጣ ስለመሆኑ ምሁራን ገልጸዋል


ፎቶ- ከገፀ ድር
ለከተማዋ ኮንፈረንስ ቱሪዝም አቅም ከሆኑት መካከል የዓድዋ ድል መታሰቢያ አንዱ ነው

**በደረጀ ታደሰ**

የኮንፈረንስ ቱሪዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙ ዘርፎች መካከል ይጠቀሳል።

ለዘርፉ ዕድገት የሚጠበቅባቸውን የሠሩ፣ ያላቸውን ዕድልና ጸጋ አውቀው ወደ ጥቅም የለወጡ ከጭስ አልባው ኢንዱስትሪ አትራፊ ሆነዋል፡፡ የከተሞች ወሳኝ ሃብት በሆነው የኮንፈረንስ ቱሪዝም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የዓለም ታላላቅ ከተሞች የጥቅል ኢኮኖሚ ዕድገታቸው ከፍተኛውን ድርሻ የሚያስገኝላቸው እስከመሆን ደርሷል፡፡ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ የመጠቀም ዕድልና ጸጋ ከተጎናጸፉ ጥቂት የዓለም አገራት ከተሞች መካከል፡-

ወደ ገጽ 9 ዞሯል




# ከባዶ ከመጀመር ልምምድ ምን ተማርን?

- ኢትዮጵያ የቀደሙ አዎንታዊ ስኬቶችን እያስቀጠለች እና በላዩ ላይ ደምራ በመሄድ ጠንካራና የበለፀገች ሀገር መገንባት ላይ አተኩራ እየሰራች ነው

**በቶለሳ መብራቴ**

ኢትዮጵያ በታሪኳ ረጅም የሀገርነት ዕድሜና ታላቅ የሥልጣኔ ዘመናት ቢኖሯትም፣ የታሪክና የፖለቲካ ምዕራፎቿ ግን ብዙ ጊዜ የቅብብሎሽ ሳይሆን የመቆራረጥና የዜሮ ድምር አዙሪት ሰለባ ሲሆኑ ይታያሉ። እስካሁን ባለፍንባቸው ሥርዓት-መንግስታት የቀደመውን ሙሉ በሙሉ በማፍረስና "ታሪክ በእኔ ካልተጀመረ?" በሚል የተሳሳተ አካሄድ ሀገሪቱን በአብዛኛው በሚባል ደረጃ ከባዶ መነሻ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የመንግሥት ምስረታው፤ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ትልቅ ምዕራፍ ነው!

አንድ ትልቅ ሀገር የሚገነባው ትልቅ ርዕይ ባለው ትልቅ ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያም ዛሬ የምትገኝበት ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ይህንኑ እውነት በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል። ሕዝቡ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ በሰጠው ድምፅ የራሱን የፖለቲካ ምርጫ ካሳየ በኋላ፣ የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ተመስርተው፣ አዲስ መንግሥት መመሥረቱ በሕዝብ ይሁንታ ላይ የተመሠረተ የተቋማዊ ቅብብሎሽና የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደትን የሚያጠናክር ትልቅ ምዕራፍ ነው። የዚህ ሂደት ትርጉም ግን በምርጫ ውጤትና በሹመት ቁጥር ብቻ የሚለካ አይደለም። ሀገረ መንግሥት ትናንት የተገነባውን ጠቃሚ መሠረት ጠብቆ፣ ዛሬ የሚጎድለውን ሞልቶ፣ ለነገ የሚያስፈልገውን በላዩ ላይ መደመር ነው። የሀገር ግንባታ የትውልድ ቅብብሎሽ ነው፤ አንዱ ትውልድ የጀመረውን ሌላው ሳያጠፋ በላዩ ላይ በላቀ ደረጃ የራሱን አሻራ የሚያኖርበት ሂደት ነው። ይህ እሳቤ ከመደመር ፍልስፍና ጋርም የሚቆራኝ ነው። የቀደመውን ሁሉ መቀበል ሳይሆን፣ መልካሙን ማስቀጠል፣ የጎደለውን መሙላትና ዘመኑ የሚጠይቀውን አዲስ እውቀትና ልማት መጨመር ነው።

በዚህ መሠረት የአዲሱ መንግሥት ምሥረታ ዋነኛ ፈተና ማን ተሾመ? ማን ምን የሥልጣን ቦታ ያዘ? ከሚለውም በላይ ነው። ዋናው ጥያቄ "እነዚህ አመራሮች የሕዝቡን ይሁንታ ወደ ተጨባጭ የብልፅግና፣ የሰላም፣ የፍትሕና የመልካም አስተዳደር ውጤት እንዴት ይቀይሩታል?" የሚለው ነው። የሕዝብ ድምፅ የአምስት ዓመት የአደራ ውል ነው። ሹመትም የሕዝብ አደራን በትጋት ለመሸከም የሚሰጥ ኃላፊነት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በአዲሱ መንግሥት ምሥረታ ወቅት ሹመት ለህዝብ ጥቅም የሚፈጋበትና ኢትዮጵያን ወደ ሥልጣኔ ለማስኬድ የሚሠራበት አደራ መሆኑን አጽንዖት ሰጥተዋል።

እዚህ ላይ የአዲሱ ካቢኔ አወቃቀር የሚያስተላልፈው ሌላ ጠቃሚ መልዕክት አለ። ከ22 የካቢኔ አባላት 9ኙ ሴቶች መሆናቸው፣ የተለያዩ ሙያዊና ማኅበራዊ ተሳትፎዎችን ማካተቱ የአመራር ብቃትን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ትክክለኛውን የኢትዮጵያ መልክና ወቅቱ የሚጠይቀውን የፖለቲካ ልምምድ ከፍታ ከግምት ያስገባ መሆኑን እንረዳለን። ይሁንና አካታችነት በቁጥር ብቻ አይረጋገጥም፤ በውጤት ነው የሚመዘነው። ተቋማትም በሕግ፣ በአሠራርና በተቋማዊ እሴት መመራት አለባቸው። ጠንካራ ሀገር የሚገነባው ተቋማትን በማጠናከር ነው። ኢትዮጵያ የምትፈልገው በትውልድ ላይ የሚደመር፣ የሚጠናከርና የሚተላለፍ ሥርዓት ነው። ትልልቅ ፕሮጀክቶች፣ የሰው ኃይል፣ የኢኮኖሚ አቅም፣ የዲፕሎማሲ ተሞክሮና ተቋማዊ እውቀት የሀገር የጋራ ሀብቶች ናቸው። የሀገረ መንግሥት ግንባታ በተቋማት አቅም፣ በዲሞክራሲያዊ ባህል፣ በሰላማዊ የሥልጣን ቅብብሎሽና በዜጎች ተሳትፎ ይመዘናል። ስለዚህ 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የሕዝብ ድምፅ ውጤትን ወደ ተቋማዊ አፈጻጸም በመቀየር ይለካል። በዚህ መንገድ ምክር ቤቱ የሕዝብ ውክልናን ወደ ሕግና ቁጥጥር ማሸጋገር፣ አስፈጻሚው አካል ደግሞ የሕዝብን ፍላጎት ወደ ተጨባጭ አገልግሎትና ልማት መቀየር ይጠበቅበታል።

አዲሱ መንግሥት ከሁሉ በፊት ሊያስታውሰው የሚገባው ታላቅ እውነት ሥልጣን ጊዜያዊ ነው፤ ሀገር ግን ዘላቂ ናት። ሹመት ይመጣል፣ ይሄዳል፤ የሚቀረው የተገነባው ተቋም፣ የተሻሻለው ኑሮ፣ የተጠበቀው ሰላም፣ የተጠናከረው ሉዓላዊነትና ለቀጣዩ ትውልድ የተላለፈው አቅም ነው። ስለዚህ አዲስ የተሾሙ አመራሮች የሕዝብን አደራ እንደ ታሪካዊ ኃላፊነት ሊመለከቱት ይገባል። ዛሬ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በታማኝነት፣ በብቃት፣ በተጠያቂነትና በጋራ ሥራ ካከናወኑ፣ የመንግሥት ምሥረታው ለትውልድ የሚሻገር ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ የሚያስቀጥል ታላቅ ምዕራፍ ይሆናል።

## የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## በትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የድምፅ ብክለት ቢወገድ?

ሳሮን ከጊዮርጊስ

በሕዝብ ትራንስፖርት እና በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች ስንጠቀም ሁሉም እኩል መብትና ግዴታ እንዳለው እሙን ነው፡፡ ነገር ግን በትራንስፖርት አማራጮች የተሳፋሪዎችን መብት ከሚያሳጡ፤ ሰላምና ምቾት ከሚነሱ አላስፈላጊ ድርጊቶች መካከል የድምፅ ብክለት አንዱ እና ዋንኛው ነው። እነዚህም በአሽከርካሪዎች ወይም በረዳቶች አማካኝነት ያለ ተሳፋሪዎች ፍላጎት የሚከፈቱ ከፍተኛ ድምፅ ያላቸው ሙዚቃዎች፣ የሬድዮ ፕሮግራሞች፣ ሃይማኖታዊ ስብከቶች ዋንኞቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ድምፆች በትራንስፖርት አማራጭ ተጠቃሚ የሆኑ ተገልጋዮች እድሜ፣ ፆታን እና የጤንነት ሁኔታን ያላገናዘቡ መሆናቸው ደግሞ ችግሩን ያባብሰዋል፡፡

ሌላው የትራንስፖርት ተጠቃሚውን ሰላም እና ደህንነቱን የሚያውከው የመኪናው ሞተር፣ የጭስ ማውጫ (ኤክዞስት) ወይም ሌላ የውስጥ አካል ብልሽት በሚኖርበት ጊዜ ከፍተኛና አስፈሪ ድምፅ ይፈጠራል፡፡ በሚወጣው ከፍተኛ የተቃጠለ ነዳጅ ሽታም የሚደረሰው መታወክ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ አንዳንዴ ይህንን እንደተሳፋሪ ስመለከት "የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ እና የብቃት ማረጋገጫ(ቦሎ) እንዴት እና በምን መመዘኛ ተሰጠው?" የሚል ሀሳብ በውስጤ ይመላለስብኛል፡፡

ተሳፋሪው የሚፈጥረው የድምፅ ብክለት ሌላው በትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ የሚደርስ የሰላም፣ የምቾትና ደህንነት እክል ነው። በተለይ ከሞባይል ስልክ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው ችግር አንዱ ሲሆን፤ አንዳንድ ተሳፋሪዎች በከፍተኛ ድምፅ ማውራት፣ የጆሮ ማዳመጫ ሳይጠቀሙ የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን መጠቀም፤ እንዲሁም ሀይማኖታዊ መዝሙሮችን፣ ሙዚቃዎችን እና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን ማዳመጥ ተጠቃሽ ናቸው።

አንድ ተሳፋሪ የትራንስፖርት አማራጮቹ ሰላሙን እና ደህንነቱ ጠብቀው በአግባቡ ሊያገለግሉት ሲገባ ነገር ግን ባለሙያዎች እንደሚያስቀምጡት በከፍተኛ ድምፅ ጤናው ይረበሻል። በተሳፋሪዎችና በአሽከርካሪዎች መካከልም አለመግባባት እና አላስፈላጊ ጭቅጭቆችን ይፈጥራል። ከልክ በላይ ድምፅ መኖሩ አሽከርካሪው ላይ የትኩረት መበተን በማስከተል ለትራፊክ አደጋ መንስኤም ሊሆን ይችላል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በርካታ ሀገራትና ከተሞች በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ላይ ከፍተኛ ድምፅ ማውጣትን በሕግ ይከለክላሉ። በእኛ ሀገር እና በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ የድምፅ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ወጥተው በሥራ ላይ እንዲውሉ መወሰኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ሕጎቹ ከወረቀት አልፈው ወደ ተግባር መለወጥ ላይ ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ የወጡ ሕጎች ወደ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉም ተፈጻሚ የሚሆኑበት አሠራር መፈጠር ይገባዋል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ተሳፋሪም የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም የሚፈልጉትን ድምፅ ለመስማት የጆሮ ማዳመጫዎችን መጠቀም አለባቸው፡፡ አሽከርካሪዎችም የመኪናቸውን የድምፅ ማገጃዎችና የሞተር ሁኔታ በየጊዜው መፈተሽ የሚኖርባቸው ሲሆን የተሽከርካሪ ጥገና ማድረግ ለራስም ለንብረትም እንዲሁም ለተሳፋሪ መትረፍ ነውና ትኩረት ቢደረግ፡፡

የሚመለከተው አካልም እነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ በሚያደርግበት ወቅት ክፍተቶቹ በደንብ ቢታዩ ሌላው አስተያየቴ ነው። የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ጉዳይ የተሳፋሪም ሆነ የአሽከርካሪ ጉዳይ እንደመሆኑ ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ እና ተደማምጦ አለፍ ሲልም የሚመለከተው አካል ተገቢውን ህግ አስቀምጦ ሰላምና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት መስጠትና መገልገል ተገቢነት አለው እላለሁ፡፡ እናንተስ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ፋንታነሽ ተፈራ
ሽዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

# ኢትዮጵያ... ከገጽ 1 የዞረ

ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላና በረሃ ልዩ ልዩ የአየር ንብረት ያለባት ዐይነ ግቡ ምድር፤ ጠይም፣ የቀይ ዳማው፣ ጥቁርና ቀዩ ሁሉም በየመልኩ፣ ሁሉም በየልኩ የሚኖርባት ግሩም ሀገር መሆኗን ብዙዎች በየዘመናቱ ቢመሰክሩላትም፣ ይህንን ሀብቷን በወጉ ገልጣ፣ አልምታና አስተዋውቃ በተገቢው አለመጠቀሟን እየጠቀሱ በቁጭት ጅራፍ የሚገርፏትም አያሌ ናቸው፡፡

ከዓመት እስከ ዓመት የሚፈስሱ ወንዞች፣ ቢቆፍሩ ወርቁን፣ ቢያርሱ እሸቱን እንደልብ የሚያፍሱበት የሰጡትን የሚያበቅል መሬት፣ ሀገሩ በጠላት ስትነካ እንደ አራስ ነብር የሚወረወር፣ እንደ ዓድዋ ሁሌም የሚከበር፣ ቢሠራ አገር የሚያኮራ፤ ታጋሽ፣ ጀግናና ታታሪ ሕዝብ . . . ይሄ ሁሉ እያላት ግን ለቁጥር የሚያታክቱ የመከራ ቀንበሮችን ተሸክማ መድረሻው በማይታወቅ እና አዋጭ ባልሆነ መንገድ ስትኳትን ኖራለች፡፡

የመደመር መንግሥት ግን ይህንን አድካሚ መንገድ የቀየረው ይመስላል። ለአብነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባሳለፍነው ሰኞ የአዲሱ የመደመር መንግሥት ምሥረታ መርሃ ግብር ላይ፣ “የመጣንባቸው መንገዶች ከተጋን ህልማችንን መኖር እንደምንችል ያረጋገጡ ናቸው” በማለት የገለፁትን ጥልቅ እሳቤ ቦታ ሰጥተን፣ ባለፉት ዓመታት በቱሪዝም፣ ማዕድን፣ ኢንዱስትሪ፣ ቴክኖሎጂ እና ግብርና... ላይ የተገኙ ውጤቶችን ይዘን፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ ዓመታት አሳካቸዋለሁ ብላ ለተያያዘቻቸው ተረጂነትን የማስቀረት፣ ከድህነት የመውጣትና የአፍሪካ ተምሳሌት ሀገር የመሆን ውጥኗ በትጋት ከተሠራ ማሳካት እንደሚቻል እንረዳለን፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ይንገስ ዓለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ሀገር ጸጋን፣ የሰው ኃይልን፣ እውቀትን፣ ውሃን እና ቴክኖሎጂን በማቀናጀት ግብርናውን ወደ ዘመናዊና ተወዳዳሪ ዘርፍ መቀየር ተችሏል፡፡

በዚህም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው አማካኝነት ለዘመናት ስንዴ ስትቀበል የነበረችው ሀገር፣ የስንዴ ልማትን በማስፋፋት የምግብ ሉዓላዊነቷን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ጀምራለች። በተጨማሪም በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር በእንቁላል፣ ዶሮ፣ ማር፣ ወተትና አሳ ሀብት ልማት የዜጎች ተጠቃሚነት ሲያድግ፤ በአረንጓዴ ዐሻራ የተተከሉ ችግኞች ደግሞ ለአካባቢ ጥበቃ እና ለፍራፍሬ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።


ፎቶ:- ከገጸ ድር
ኢትዮጵያ በግብርና፣ በህዳሴው ግድብና ሌሎች የልማት ስራዎች ያገኘቻቸው ውጤቶች እየተገነቡ ላሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች መሠረት ይጥላሉ

በኢንዱስትሪው ዘርፍም ከዚህ ቀደም የነበሩትን እንደ የኃይል መቆራረጥ እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ያሉ ማነቆዎችን በመፍታት የማኑፋክቸሪንግ የማምረት አቅም ከ47 በመቶ ወደ 67 በመቶ ማደግ ችሏል፡፡ ለዚህም የ“ኢትዮጵያ ታምርት” ንቅናቄ ተዘግተው የነበሩ ፋብሪካዎችን ወደ ሥራ በመመለስ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በሌላ በኩል፣ በማዕድን ዘርፍ እንደ ወርቅ፣ ብረት እና እብነ-በረድ ያሉ ተፈጥሮአዊ ጸጋዎችን በጥሬው ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ በማቀነባበር ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተጀምሯል፤ ይህም የውጭ ምንዛሬ ገቢን ከመጨመሩ ባሻገር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እያስቻለ ነው፡፡

በቤተ መንግሥት (በአንድነት ፓርክ) ከተጀመረው ልማት እስከ ‘ገበታ ለሸገር’ (እንደ እንጦጦና ወዳጅነት፣ አራዳ እና ሸገር ፓርኮች)፣ ‘ገበታ ለሀገር’ (ወንጪ፣ ኮይሻ፣ ጎርጎራ) እና ‘ገበታ ለትውልድ’ ፕሮጀክቶች መላ ሀገሪቱን ያቀናጁ የቱሪዝም መዳረሻዎች ተፈጥረዋል። በቴክኖሎጂው ዘርፍም የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት መቋቋም ሀገሪቱን የአፍሪካ የቴክኖሎጂ አቅጣጫ መሪ አድርጓታል።

በእርግጥም ሀገር ትናንት ያለፈችባቸው መንገዶች፣ ዛሬ ያሳካቻቸው ተጨባጭ ልማቶች እና ከፍ ያሉ የወደፊት ህልሞቿ የአንድ ሀገርና መንግሥት የመቻል አቅም መለኪያዎች ናቸው፡፡ ይህንን ያሉት ደግሞ የማኅበረሰብ ጥናት እና የምጣኔ ሀብት ተመራማሪው ጃዊድ ናዋቢ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

ጃዊድ ናዋቢ (ዶ/ር) “Why States Matter: State Capacity and Economic Development” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2022 ባሳተሙት መጽሐፋቸው እንደገለጹት፤ ከተጨባጭ ሀቅ የተነሳና ሊተገበር የሚችል ፖሊሲ፣ የመንግሥት አቅም፣ ተግባራዊ አፈጻጸም፣ በውጤት የሚለካ ለውጥና ቀጣይነት ያለው ልማት የጠበቀ ትስስር አላቸው፡፡ እናም አንድ መንግሥት በትናንት ጽናቱና ብርታቱ፣ በዛሬ ድካሙና ውጤቱ፣ ያልተሄደበትን ደግሞም አዋጭና አትራፊ መንገድን በመምረጡ እንዲሁም ሊጨበጥ በሚችል ህልሙ ይመዘናል፡፡

ለመሆኑ ከላይ በጠቀስናቸውም ሆነ በሌሎች መመዘኛዎች የመደመር መንግሥት ምን ይመስላል? የሚለውን ሀቅ በምሁራን ምልከታ እና በተጨባጭ ሀቆች ላይ ተንተርሰን እንፈትሻለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከመደመር መንግሥት በፊት የነበሩ መንገዶችንም መመልከት አይከፋም፡፡ አዎ፣ ኢትዮጵያ በረጅም የታሪክ ጉዞዎቿ ውስጥ ቀላል የማይባሉ ምዕራፎችን በብዙ ስቃይ ውስጥ አሳልፋለች፡፡ ወደ ከፍታዋ ደረሰች ሲባል ስትመለስ፣ ወጣች ሲባል ስትጠልቅ፣ ተሻገረች ሲባል ድንገት በሚመጡ ማዕበሎች ወዲያ ወዲህ ስትማስን ዘመናት ነጉደዋል፡፡

ለሕመሟ ፈውስ ይሆን ዘንድ የምትወስዳቸው መድኃኒቶች ደግሞ የተለመዱና ሁሉንም ሕመም የማይፈውሱ እንደነበሩ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ዛሬ ግን ኢትዮጵያ በአዲስ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህ እውነት ታላላቅ የሚባሉ አብነቶችን ማንሳት ይቻላል የሚሉት የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አሕመድ ሰይድ፤ እንደ ሀገር እንቅፋት የሆኑብንን ችግሮች በምክክር ለመፍታት የሄድንበት ርቀት፣ የሀገር በቀል ኢኮኖሚው በለውጥ ምዕራፍ ላይ መሆኑን፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በአገልግሎትና መሰል ዘርፎች ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን፣ እንዲሁም የሀገርን ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ ልቦናዊና መሰል ከፍታዎች ማሳያ የሆነውን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ለፍጻሜ ማድረሱ በትክክልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም የመጣንባቸው መንገዶች ከተጋን ህልማችንን መኖር እንደምንችል ያረጋገጡ ናቸው፡፡

ታሪክ እንደሚነግረን በኢትዮጵያ ባለፉት የመንግሥት ሥርዓቶች የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘቡ የኢኮኖሚ ሞዴሎች በመተግበራቸው የሚፈለገውን ያህል እድገት እንዳይመዘገብ አድርጎ ቆይቷል፡፡ ይህ መንገድ ዛሬ የዓለምን ሀቅ በያዘ ደግሞም ሀገር በቀል ለሆኑ እሳቤዎች ቦታ በሰጠ በመደመር እሳቤ ተቀይሯል፡፡

ለአብነትም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተጻፈው መደመር መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸውና በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫ እንደሚያመለክተው የመደመር መንግሥት የሚከተለው የትብብር ሞዴልን ነው፡፡ በዚህ ሞዴል የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ ተገቢውን ሚና ይጫወታል፣ ይደገፋል እንዲሁም ይበረታታል፡፡ መንግሥት ደግሞ በሥራ ፈጠራ እሳቤ የግሉ ዘርፍ በማይደፍራቸው ዘርፎች ላይ እንዲሳተፍና ከግሉ ዘርፍ ጋር በጋራ በማልማት፣ አዳዲስ ሀሳቦችን በማመንጨት እና አዳዲስ የኢኮኖሚ ዘርፎችን እየፈጠረ መሆኑን ባለፉት ዓመታት በአገልግሎት፣ በቱሪዝም፣ ማዕድን፣ ኢንዱስትሪ፣ ቴክኖሎጂና ግብርና በመሳሰሉ ዘርፎች የተመዘገቡ ውጤቶች ምስክር ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከመደመር መንግሥት በፊት በነበሩት ዘመናት ከሌሎች ሀገራት የተቀዱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እና ሥርዓቶችን ከሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሳታጣጥም መተግበሯ የዜጎቿ የኑሮ ደረጃ እንዳይሻሻል አድርጎ መቆየቱ እና አሁን በመደመር እሳቤ ወደ ስልጣኔ ምዕራፍ እየተሸጋገረች መሆኑን በሚያመላክት መልኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአዲሱ የመደመር መንግሥት ምሥረታ ላይ ንግግር ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋር ቆይታ ያደረጉት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አሕመድ ሰይድ፣ ኢትዮጵያ በተምሳሌትነት ምዕራፍ ላይ መሆኗን ጠቅሰው፣ ዛሬም የመደመር መንግሥት ያስቀመጣቸውን እነዚህ ወሳኝ እና ሀገራዊ ጉዳዮች እንዳለፉት ዓመታት በትጋት ከተሠራባቸው ማሳካት እንደሚቻል እስካሁን በተለያዩ ዘርፎች የተመዘገቡ ለውጦች ማሳያ ናቸው፡፡

# ከባዶ... ከገጽ 1 የዞረ

መስመር እንድትነሳ ሲያደርጋት ቆይቷል።

የዓለም ሀገራት የሥልጣኔ ከፍታን የተጎናፀፉት፣ ዘመናትን በሚሻገር ተቋማዊ ቅብብሎሽ፣ የቀደሙ ስኬቶችን አጠናክሮ በመያዝ እና በበጎ መሠረቶች ላይ አዳዲስ ድሎችን በመገንባት እንጂ በእያንዳንዱ ዘመን መባቻ የቀደመውን አፍርሶ ከባዶ በመጀመር አይደለም።

በዓለማችን ታሪክ ታላላቅ ሀገራት የተገነቡት፣ የታፈረና የተከበረ መንግሥት መመሥረት የቻሉት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ በሚተላለፍ አዎንታዊ የዕውቀት፣ የተቋማትና የብሔራዊ ጥቅሞች የማስቀደም እሳቤዎች ቅብብሎሽ ነው።

የሰው ልጅ ሥልጣኔ መሠረቱ የቀደመው ትውልድ የጣለውን ድንጋይ ሳይነቅሉና ሳይሰብሩ፣ በላዩ ላይ ሌላ ድንጋይ ደርቦ ሁለንተናዊ ዕድገትን ማረጋገጥ ነው። በአንፃሩ አዎንታዊ የትውልድ ቅብብሎሽ ባልተጠበቀበት፣ የነበረው ተቋማዊና ማህበራዊ ሀብት በየጊዜው በሚናድበትና በሚበተንበት ማህበረሰብ ውስጥ የራቀውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማሳካት ከቶ አይታሰብም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር መንግሥት ምሥረታ በተከናወነበት 7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር "አንዱ ትውልድ የሰበሰበውን ሌላኛው እየበተነው፤ አንዱ የገነባውን ሌላኛው እያፈረሰ፣ መነሻ ወረት እያጠፋን ከባዶ እየጀመርን መሰልጠን የሚባል ነገር ከቶ አይታሰብም" ማለታቸውም ከዚሁ መነሻነት ነው፡፡

የዚህን ታሪካዊና መዋቅራዊ ስብራታችንን ጥልቅ ህመም የሚያሳይና ለሀገራዊ ማገገም የቀረበ ታላቅ ጥሪ ነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር። ይህ መርህ የሀገራችንን ያለፈ ታሪክ ክፍተቶች የሚፈትሽ ብቻ ሳይሆን፣ አሁን በምንገኝበት የወቅታዊ ፖለቲካና የሀገር ህልውና ምዕራፍ ውስጥ የሚታዩ አደገኛ አዝማሚያዎችን የሚሞግት፣ እንዲሁም የመደመር አስተሳሰብ ለጠንካራ ሀገር ግንባታ የሚያበረክተውን ሚና በግልጽ የሚያመላክት ትልቅ እይታ ነው። ከቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ወደ ደርግ፣ ከደርግ ወደ ኢህአዴግ የተደረጉት የሥልጣን ሽግግሮች በሰላማዊና ተቋማዊ ቅብብሎሽ ሳይሆን የቀደመውን በሙሉ አፍርሶና ኮንኖ ከባዶ በመጀመር የታጀቡ ናቸው። ንጉሱ የገነቡት ተቋማዊ፣ ህጋዊና ዲፕሎማሲያዊ መዋቅር በደርግ ሰንሰለት ፈረሰ፤ ደርግ ያስቀመጣቸው የሀገር መከላከያ፣ የኢንዱስትሪና የሰው ኃይል መዋቅሮች ደግሞ በቀጣዩ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ እንዲበተኑ ተደረገ።

ይህ አፍራሽ ባህል ሀገሪቱ ሁልጊዜ በመነሻ መስመር ላይ እንድትቆም በማድረግ የልማትና የስልጣኔ ጉዞዋ እንዳይሰምር አድርጎታል። ትውልዱ የቀደመው ትውልድ ያቆየለትን መልካም ወረት ይዞ ወደፊት ከመራመድ ይልቅ፣ የቀደመውን በመርገምና በማፍረስ ጊዜውንና ጉልበቱን ሲያባክን ኖሯል። ይህን በጉዳዩ ዙሪያ ሙያዊ ማብራሪያ የሰጡን ባለሙያዎችም ያረጋግጣሉ፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ አብዲበሽር ሰኢድ (ዶ/ር)



ፎቶ- ከገፀ ድር

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አበራ ሄብሶ

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ አበራ ሄብሶ፣ ሀገርን በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት የነበሩ ወረቶችንና የጋራ እሴቶችን አጠናክሮ ማስቀጠል አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል። በሀገራችን አንዱ የገነባውን ሌላው እያፈረሰ ከባዶ የመጀመር አዙሪት እንዲፈጠር ያደረጉ ሁለት ዋና ምክንያቶችን አንስተዋል። እንዚህም፤ የኢትዮጵያን እድገትና ብሔራዊ ፍላጎት የማይፈልጉ ኃይሎችን ለይቶ አለማወቅ እና የሀገርን ሉዓላዊነትና የትውልድ መቀጠል ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ፍላጎት በላይ አድርጎ አለመመልከት መሆናቸውን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያውያን ከሚለያዩአቸው ይልቅ የሚያስተሳስሯቸው የጋራ ማንነቶች፣ የደም፣ የባህል፣ የቋንቋና አብሮ የመኖሪያ ታሪኮች የበዙ በመሆናቸው፤ እነዚህን እሴቶች ከመሸርሸር መጠበቅ እንደሚገባ ተመራማሪው ገልጸዋል። ጠንካራ ሀገርን መገንባት የሚቻለው ከቡድንና ከግል ጥቅም ይልቅ የህዝብንና የትውልድን ዘላቂ ጥቅም ማስቀደም ሲቻል መሆኑን በመጠቆም፣ ከውጭ ጠላቶች ጋር በመተባበር ሀገርን ለማዳከም የሚደረጉ አፍራሽ አካሄዶች ከጊዜያዊ ዝንባሌ የሚመነጩና የውርደት ጥግ መሆናቸውን አብራርተዋል። በመሆኑም ፖለቲከኞች፣ ተመራማሪዎች፣ ምሁራን፣ የሃይማኖት አባቶችና ሙሉ የሀገሪቱ ዜጎች በጋራ በመቆም ብሔራዊ ጥቅሞቿን ለማስከበር በቁርጠኝነት መስራት እንዳለባቸው አመላክቷል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ አብዲበሽር ሰኢድ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜያት ነገሮችን ከዜሮ የመጀመር ልምምድ ሲንጸባረቅ የቆየ ሲሆን፣ በፖለቲካው መስክ ተቃውሞንም ሆነ ድጋፍን በምክንያትና በልክ የማድረግ ችግር መኖሩ የቀደመውን አካል በመቃወም ብቻ እሱ የሰራው ነገር በሙሉ መፍረስ አለበት የሚል የተሳሳተ እይታ እንዲገነባ ማድረጉን አስረድተዋል። ይህ ከባዶ የመጀመር አዙሪት በሀገራችን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ የጎላ ነው የሚሉት መምህር አብዲበሽር (ዶ/ር)፣ ተቋማት የህግና የአሰራር የበላይነት ያላቸው ሳይሆኑ የሰዎች ወይም የፓርቲዎች መለወጫ እየሆኑ አጠናክሮ የመቀጠል አቅማቸውን አጥተዋል። በየጊዜው በሚደረጉ የፖለቲካ ለውጦች ምክንያት ተቋማዊ ትውስታ እየጠፋ ከዜሮ እንዲጀመሩ ተገደዋል ሲሉ አክለዋል።

በአንድ ትውልድ ድካምና በሕዝብ ሀብት የተገነቡ ታላላቅ ፕሮጀክቶች፣ መሠረተ ልማቶችና መዋቅሮች በፖለቲካ ቂም በቀልና በመርህ አልባነት ምክንያት እንዲወድሙና እንዲተው ተደርገዋል። ይህም ሀገሪቱ በኢኮኖሚ በታችኛው ደረጃ ላይ ተዘፍቃ እንድትቀር አድርጓታል። ታሪክን የትውልድ ቅብብሎሽ መስመር አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ የፖለቲካ መፋቂያ ማድረግ፣ ትውልዱ ከቀደሙ ስህተቶች እንዳይማርና ስኬቶች እንዳይቀጥል ትልቅ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን መምህር አብዲበሽር (ዶ/ር) ተናግረዋል።

እንደ አብዲበሽር (ዶ/ር) ገለጻ፣ አሁን ላይ በመንግሥት ከተያዙ ዋና ዋና የአስተሳሰብ መሠረቶች መካከል የመደመር ፍልስፍና ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። የመደመር እሴት መነሻ ሃሳብ፣ ያለፈውን በሙሉ ማፍረስ ወይም ሁሉንም ነገር እንዳለ መቀበል ሳይሆን መልካሙን ማስቀጠል፣ የጎደለውን መሙላት እና የዘመኑን አዲስ እውቀትና ሀሳብ ማዕከል ነው። ይህ አስተሳሰብ ሀገር በየጊዜው ከሚደርስባት የዜሮ ድምር አዙሪት ተላቅቃ በፅኑ መሠረት ላይ እንድትቆም የማስቻል አቅም ያለው ሀገራዊ አስተሳሰብ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ሀገር የምትገነባው ያለፈውን መልካም ነገር እያስቀጠሉ፣ የተሳሳቱትን እያረሙ እንጂ የሚጠቅመውንም የማይጠቅመውንም እየነቀሉ አዲስ መሠረት በመጣል አይደለም። የፖለቲካና የትውልድ ቅብብሎሽ ማለት የቀደመውን በሙሉ መካድ ሳይሆን፣ የቀደሙት የሰሩትን አዎንታዊ ጎን መነሻ አድርጎ ያልተሰሩትን በመስራት ሀገርን ማሳደግ ነው።

ዛሬ በሀገራችን የምናየው ትልቁና አደገኛው ፈተና፣ ባለው ላይ ደምሮ የመሄድ ባህል አለመዳበሩ ብቻ ሳይሆን፣ "እኔ ካልመራሁ ሀገሪቱ ትፍረስ" የሚል አጥፊ የፖለቲካ እሳቤ ነው። አፍራሽ ሀይሎች "ለህዝብና ለሀገር እንሰራለን" በሚል መፈክር እየተንቀሳቀሱ፣ በተግባር ግን ከውጭ ጠላቶች ጋር የሚጣመሩበት አስከፊ አዝማሚያ ይስተዋላል። ይህም ከባዶ የመጀመር አስተሳሰብ የደረሰበትን የከፋ የፖለቲካ ውድቀትና አጥፊነት ያሳያል። የፖለቲካ ስልጣን ለማግኘት ወይም የራስን ፍላጎት ለመጫን ሲባል የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ መጣል፣ የታሪክ ጠበብትና ማህበረሰቡ ሊኮንኑት የሚገባ አደገኛ መስመር መሆኑን መምህር አብዲበሽር (ዶ/ር) አስምረውበታል።

መምህር አብዲበሽር (ዶ/ር) አክለውም፣ በአንድ በኩል ለሕዝብ ሙብት እንታገላለን እያሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝብ መጠቀሚያ የሆኑ አገልግሎቶችን ማውደምና ማፍረስ እርስ በእርሱ የሚጋጭና ሀገር አጥፊ አካሄድ ነው። በተጨማሪም የፖለቲካ ልዩነቶችን በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ፣ የኢትዮጵያን ሰላምና ልማት የማይፈልጉ የውጭ ኃይሎችን ድጋፍ በመፈለግ የሀገርን ሉዓላዊነትና ህልውና አደጋ ላይ መጣል የዚሁ እኩይ አስተሳሰብ ጥግ ነው።

ኢትዮጵያ ከገጠማት የታሪክና የፖለቲካ ፈተና ወጥታ የጠንካራ ሀገርነት ማዕረግ እንድትቀዳጅ ከተፈለገ፣ ከሁሉም በላይ "ሀገርና ህዝብ ይበልጣል" የሚል አስተሳሰብ ይጠይቃል። ይኸውም የነበረውን አክብሮ የማስቀጠል፣ የጎደለውን የመሙላትና የዘመኑን አዲስ እውቀት የመጨመር ባህልን ማሳደግ ነው። ፖለቲካን የሞትና የሽረት ወይም የዜሮ ድምር ጨዋታ አድርጎ ከመመልከት ወጥቶ፣ የሀገርን የጋራ ጥቅም ማዕከል ያደረገ ተፎካካሪነትን ማዳበር ይገባል። በሀገር ህልውና፣ በሉዓላዊነት፣ በመሠረተ ልማቶችና በተቋማት ጥንካሬ ላይ አገራዊ መግባባት መፍጠር እንደሚያስፈልግ አብዲበሽር (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ወደፊት መራመድ የምትችለው የትናንቱን በጎ ጎን አክብራ፣ የዛሬውን አጠናክራና የነገውን አዳዲስ ሀሳብ አክላ ስትራመድ ብቻ ነው። የትውልድ ቅብብሎሽ ማለት የቀደመውን አፍርሶ አዲስ መገንባት ብቻ ሳይሆን፣ የቀደመው የጣለውን መሰረት ተንተርሶ ማሳደግ ነው። ከባዶ የመጀመርን አውዳሚ አዙሪት ሰብረን መውጣት ካልቻልን፣ ለትውልድ የሚሻገር ጠንካራ ሀገርና የተረጋጋ ሥርዓት መገንባት አይቻለንም። አፍራሾች ለሀገር እንሰራለን እያሉ ከሀገር ጠላት ጋር የሚጣመሩበትና ወረትን የሚያጠፉበት አካሄድ በቃ ሊባል ይገባል። መነሻ ወረታችንን ሳናጠፋ፣ ባለው ላይ እየደመርንና እያደስን ከሄድን ብቻ ኢትዮጵያን የታፈረች፣ የበለፀገችና ለትውልድ የምትሻገር ጠንካራ ሀገር አድርጎ መገንባት ይቻላል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
## ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበው ያጸደቋቸው የመደመር መንግሥት ካቢኔ አባላት



### አቶ ተመስገን ጥሩነህ
### የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር



ጌዲዮን ጢሞቲዮስ (ዶ/ር)
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር



አዲሱ አረጋ (ዶ/ር)
የግብርና ሚኒስትር



ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)
የገንዘብ ሚኒስትር



መሃመድ እድሪስ
የመከላከያ ሚኒስትር



ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)
የትምህርት ሚኒስትር



ሃና አርአያሥላሴ
የፍትሕ ሚኒስትር



ያስሚን ወሃብረቢ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር



ፍስሃ ይታገሱ (ዶ/ር)
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር



ሃብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)
የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትር



ዶክተር መቅደስ ዳባ
የጤና ሚኒስትር



አወሉ አብዲ
የሥራና ክህሎት ሚኒስትር



አይናለም ንጉሴ
የገቢዎች ሚኒስትር



በረከት ፍስሃጽዮን
የብሔራዊ ስትራቴጂ ሚኒስትር



ሰላማዊት ካሳ
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር



ዓለምጸሃይ ጳውሎስ
የማዕድን ሚኒስትር



ሳዳት ነሻ
የሎጂስቲክስ ሚኒስትር



ሻዊት ሻንካ
የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር



ሙሳ አደም
የሰላም ሚኒስትር



ፍሬሕይወት ታምሩ
የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር



መሃመድ አብዱራሃማን (ኢ/ር)
የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር



ሱልጣን ወሊ (ዶ/ር)
የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር



አክሊሉ ታደሰ (ዶ/ር)
የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትር

# ሀገራዊ ጥቅምን ያስቀደመው የፖለቲካ ባህል

**• ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር አብሮ የመሥራትና ሥልጣን የማጋራት ልምድ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ምሁራን ገልጸዋል**



ፎቶ፡- ከገፀ ድር

በመንግስት ምስረታው የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮችም ሹመት አግኝተዋል

**በስንታየሁ ምትኩ**

በምርጫ ያሸነፈ የፖለቲካ ፓርቲ የመንግስትን ቁልፍ ስልጣኖች ሙሉ በሙሉ በብቸኝነት በመያዝ ውሳኔዎች የሚያሳልፍበት፤ ተፎካካሪዎች ደግሞ ወደ ዳር ተገፍተው የሚታዩበት ሁኔታ የፖለቲካችን መገለጫ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከባለፈው አምስት ዓመት ጀምሮ በምርጫ ያሸነፈው ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን "ተፎካካሪ" ብሎ ከመጥራት ጀምሮ በመንግስት ምስረታ ስልጣን በማጋራት አካታችነት የታየበት አዲስ የፖለቲካ ባህል እንዲፈጠር እየሰራ ይገኛል፡፡ በፌዴራል፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በክልሎች የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ተመድበው ሀገርና ህዝብን በማገልገል ተሳትፎ ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ አሁንም እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የህዝብ ይሁንታ ያገኘው የብልፅግና ፓርቲ፤ ከሰሞኑ ባካሄደው የመንግስት ምስረታ ላይም የተለያዩ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝብ ይሁንታ ካገኘው ፓርቲ ጋር ስልጣን ተጋርተው፣ ህዝብን የሚያገለግሉበትና አብረው የሚወስኑበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የአዲሱ የመደመር መንግሥት ምሥረታ እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር መንግስት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መስራት እንደሚቻል በተግባር አሳይቷል። "ገዥው ፓርቲና ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለአንድ ሀገር፤ በአንድ መንግስት ውስጥ ሲሰሩ ያልተስማማቸው አካላት ነበሩ፡፡ ለብሔራዊ ጥቅም ግን በጋራ መስራት እንደሚቻል በተግባር አሳይተናል፡፡" ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከትናንት በስቲያም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን ይፋ አድርገዋል፡፡ በምክር ቤቱ ሹመታቸው ከፀደቀላቸው ከ22ቱ የካባኔው አባላት መካከል የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ይገኙበታል፡፡ ገዥው ፓርቲ ለተፎካካሪ ፓርቲ ስልጣን በማጋራት አብሮ እየሰራ እንደሚቀጥል በማሳያነት ከሚጠቀሱት መካከል የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አመራር በመሆን እና ባለፉት አምስት ዓመታት የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር በመሆን ያገለገሉት ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) አንዱ ናቸው፡፡ ብርሃኑ (ፕሮፌሰር) በድጋሚ የትምህርት ሚኒስትርነት ቦታ እንዲቀጥሉ የተሾሙ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ ብርሃኑ (ፕ/ር) በተመደቡበት ቦታ የመንግስትን ፖሊሲ በመፈፀም ከፍተኛ ብቃት እና ገዥውና የሚፎካከሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለብሔራዊ ጥቅምና ፍላጎት በጋራ ሊሰሩ እንደሚችሉ በተግባር ማሳየታቸውን ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው የአፋር ህዝብ ፓርቲ ሊቀ መንበር፣ በአፋር ክልል ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ለማሳተፍ በተወሰደው እርምጃ የአፋር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ በመሆን ሲያገለግሉ የቆዩት፣

**መንግስት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መስራት እንደሚቻል በተግባር አሳይቷል**

በኢትዮጵያዊነትና አብሮ በመስራት እምነት ያላቸው አቶ ሙሳ አደም የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር በመሆን ተሾመዋል፡፡ ካቢኔው ብቃትና ብዝሃነትን ማዕከል አድርጎ እንዲዋቀር ተደርጓል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደተናገሩት ገዥው ፓርቲ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ስልጣን በማጋራት አብሮ የመስራት ልምድ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ባሻገር በተለያዩ የኃላፊነት እርከኖችም ይቀጥላል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የመንግስት ምስረታ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፣ በከተማዋ በአዲሱ ምክር ቤት 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች ውክልና ያገኙ ሲሆን፣ 23 የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት እና አንድ የግል እጩ በምክር ቤቱ የመሳተፍ እድል አግኝተዋል። "የተለያየ የፖለቲካ ሀሳብ መኖሩ ጠላትነት አይደለም። በምንስማማባቸው ጉዳዮች ለጋራ ጥቅምና ለሀገራዊ ርዕይ በጋራ እንሰራለን፤ በምንለያይባቸው ጉዳዮች ደግሞ ልዩነቶቻችንን እያከበርን በሰለጠነ መንገድ እየተወያየን እንወስናለን" ብለዋል።

ከዚህ በፊት የነበረው የፖለቲካ ባህል ኋላቀር፣ ገዥውና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች አብረው መስራት የማይታሰብበትና የማይችሉበት እንደነበረ ያነሱት ከንቲባዋ፣ ስልጣን የሚያገዳድል፣ የሚያጠፋፋ ሆኖ የቆየበትን ታሪክ ከባለፈው አምስት ዓመት ጀምሮ በአዲስ ልምድ መቀየር ተችሏል፡፡ በአዲስ አበባ አዲስ የመንግስት ምስረታም የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት በካቢኔው እንዲወከሉ ተደርገዋል፡፡ አዲስ አበባ ብዝሃ ማንነት ያላቸው ህዝቦች መኖሪያ እና ህብረ-ብሔራዊነት የሚታይባት ከተማ በመሆኗ የካቢኔው አባላትም ብቃት ያላቸው፣ ብዝሃነትን ከግምት ያስገባ፣ አካታች ሆኖ መዋቀሩን አንስተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ምስረታ በከፍተኛ የኃላፊነት ስፍራ ከተሾሙት መካከል የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማት በኃላፊነት ያገለገሉት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ስራ አስፈጻሚ አቶ ግርማ ሰይፉ አንዱ ሲሆኑ፤ የኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ ተመድበዋል፡፡ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሏ ወይዘሪት ጽዮን ደረጀ ደግሞ የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ሆነው ተሾመዋል፡፡

መንግሥት አካታችና አሳታፊ የፖለቲካ ምኅዳር መፍጠሩን የገለጹት ወ/ሪት ጽዮን፤ ለአብነትም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትና በምክር ቤት ውስጥ የሚታየው የተፎካካሪ ፓርቲዎች ስብጥር የዚሁ እውነተኛ አሳታፊነት ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በገዥውና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል የርዕዮተ-ዓለም ልዩነት ቢኖርም፣ ልዩነቱ በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮችና በልማት መስክ በትብብር ከመስራት አያግድም፡፡ በመሆኑም መንግሥት

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# “የኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት ከራሷ አልፎ ለቀጣናው ሀገራት የጋራ እድገትና ደህንነት መረጋገጥ ወሳኝ ነው”

**በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ መምህር አበራ ሄብሶ**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ ሰፊ የቆዳ ስፋት፣ በአፍሪካ በህዝብ ቁጥር ሁለተኛ፣ ግዙፍ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ብትሆንም፤ ላለፉት ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ከዓለም ጋር የምትገናኝበት የባህር በር ማጣቷ ለዕድገቷና ደህንነቷ ትልቅ ፈተና ሆኖ ቆይቷል፡፡ የባህር በር ማጣት በንግድ ልውውጥ ላይ ከሚያስወጣው ከፍተኛ ወጪ በተጨማሪ፣ ሀገሪቱ በቀጣናውም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባላት ፖለቲካዊና ስትራቴጂካዊ ተፅዕኖ ላይ የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት የባህር በር ጥያቄን በቀጣናዊ፣ አህጉራዊና በዓለም አቀፍ ታላላቅ መድረኮች ላይ በግልጽ እያነሳ ይገኛል፡፡ ጥያቄው የታሪክ፣ የህግ እና የፍትሃዊነት መሰረት ያለው መሆኑን ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ማሳወቅ ከመቻሉም በላይ፤ የባህር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም እና የጋራ ልማት የሚያስፈልግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ማሳየት ተችሏል።

ለዚህም አብነቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከሦስት ሳምንት በፊት በህንድ ኒው ዴልሂ በተካሄደው 18ኛው የብሪክስ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “ለኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት ከምንም ነገር በላይ ኢኮኖሚያዊ አስገዳጅ ጉዳይ ነው፡፡ ግዙፍና እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚ ባለቤት እንደመሆናችን አስተማማኝና አማራጭ ዓለም አቀፍ የንግድ መስመሮች (የባህር በር) ተደራሽነት ያስፈልገናል፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን ፍላጎቷን በሰላማዊና በድርድር መልኩ ነው ማሳካት የምትፈልገው። ዓላማችን የንግድ ወጪን መቀነስ፣ ከፍ ያለ ችግሮችን የመቋቋም አቅምን መገንባትና የጋራ ብልፅግናን ማምጣት ነው” ብለዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ታዬ አጽቀሥላሴም ከሁለት ሳምንት በፊት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 81ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ አንስተዋል፡፡ “በታዳሽ ሀይል፣ በልማት ትስስር፣ በምግብ ዋስትና፣ በማኑፋክቸሪንግና በከተማ ልማት ስኬታማ ብንሆንም ይህንን ለማስቀጠልና ለማስፋት ዘላቂ የሆነ ቀጣናዊ ዓለም አቀፋዊ ትብብር እንፈልጋለን፡፡ ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የምናደርገው ጥረት አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የባህር በር ተደራሽነት ሳይኖር የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ የባህር በር ተደራሽነት ለሁሉም የቀጣናው ሀገራት የጋራ ጥቅምና እድገት የሚያስገኝ በመሆኑ በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን የማይናወጥ ጥያቄና ፍላጎት ለማሳካት እና ከዓለም አቀፍ የንግድ ስርዓት ጋር ለመተሳሰር ሁሉንም የዲፕሎማሲ አማራጮች በመጠቀም እየሰራች ነው” ብለዋል፡፡




ፎቶ -ከገፀ ድር
የባህር በር ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገትና ደህንነት ወሳኝ ነው

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) እና ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችም በተለያዩ ዓለምአቀፍ መድረኮች የኢትዮጵያን የባህር በር ፍላጎት እውነታ ለዓለም እያስረዱ ይገኛሉ፡፡ ሰኔ 10 ቀን 2018 ዓ.ም “ቻተም ሃውስ” የተሰኘው ዓለም አቀፍ ተቋም በለንደን ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ጌዲዮን (ዶ/ር)፤ “ኢትዮጵያ ውዝግብ በሞላበት ቀጠና ውስጥ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎቿ ቅድሚያ የምትሰጣቸው ጉዳዮች” በሚል ርዕስ ባደረጉት ንግግር፣ የኢትዮጵያ አንዱና እጅግ ወሳኝ ስትራቴጂካዊ ጥያቄ የባህር በር ማግኘት እንደሆነ ተናግረዋል። ይህ ጉዳይ አዲስ የመነጨ ፍላጎት ሳይሆን ንግድን፣ ሎጂስቲክስን፣ የኢነርጂ ደህንነትን እና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ዕቅድን እየገኣ ያለ መዋቅራዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ አቋም ግልፅ ነው፤ የባህር በር ማግኘት የሀገራዊ ልማትና የቀጣናዊ ውህደት ጉዳይ ነው፡፡

መስከረም 26 ቀን 2019 ዓ.ም በተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ የመክፈቻ ስብሰባ ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ ባደረጉት ንግግር፤ “በጋራ ተጠቃሚነትና በዲፕሎማሲያዊ አግባብ አስተማማኝ የባህር በር እንዲኖረን ያደረግነው ጥረት ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትና ይሁንታ እንዲያገኝ መሠረት መጣሉ፣ ኢትዮጵያ በጋራ የማደግና የመበልፀግ በጎ ሀሳቧን ያሳየ ነው” ብለዋል። በተያዘው በ2019 ዓመት ትኩረት ተሰጥቷቸው ከሚሠሩ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከልም የኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎት በጋራ ጥቅም፣ በሰጥቶ መቀበልና በሰላማዊ መንገድ እውን እንዲሆን ጥረት ማድረግ አንዱ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ መምህር አበራ ሄብሶ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ስልታዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላት ሀገር ናት፡፡ ሆኖም በቀጣናው ጠንካራ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆና እንድትወጣ በማይፈልጉ፣ ‘ብሔራዊ ጥቅማችን የሚረጋገጠው ኢትዮጵያ ከባህር በር ስትርቅ ነው’ ብለው በሚያስቡ የውጭ ኃይሎች በተለይም እንደ ግብፅ ያሉት በሸረቡት ተንኮል የባህር በር አልባ እንድትሆን ተደርጋለች፡፡

“ኢትዮጵያን የባህር በር ማሳጣትና ማግለል ግን ዘላቂ ቀጣናዊ ሰላም፣ መረጋጋትና የጋራ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት አያስችልም” ይላሉ የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ፡፡ ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛቷ፣ ባላት እምቅ የኢኮኖሚ አቅም፣ በሀገረ-መንግስት ግንባታ ታሪኳ እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት መስራችና መቀመጫ በመሆኗ በቀጣናው ሆነ በአህጉሩ ትልቅ አቅም አላት፡፡ ከዚህ አኳያ የባህር በር የማግኘት ጉዳይ መፍትሔ የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ በተለይም በቅርብ ጊዜያት የባህር በር የማግኘት ጥያቄዋን ብሪክስን፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በስፋት እያነሳች ትገኛለች። ይህ አካሄድ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት እየሳበና አጀንዳ እየሆነ መጥቷል። የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ እንደሚያስረዱት፤ ይህ ዓይነቱ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ መጠናከር ያለበትና ውጤታማ አካሄድ ነው። ኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄዋ ፍትሀዊ፣ በታሪክም የነበራት፣ ለጋራ ተጠቃሚነት መሆኑን በብሪክስ ጉባኤ ማንሳቷ፣ እንደ አባል ሀገርነቷ ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽና ድጋፍ ለማግኘት አጋዥ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት ሀገሪቱ እያስመዘገበች ያለው የኢኮኖሚ እድገት፣ የአፍሪካ ቀንድን በሃይል ልማት ለማስተሳሰር የምታደርገው ጥረት እና የምትከተለው ንቁ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነቷ እያደገ እንዲመጣ እያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም ቀጣናው ለዓለም አቀፍ ንግድና ደህንነት ወሳኝ ስትራቴጂካዊ አካባቢ ቢሆንም ውስብስብ፣ ያልተረጋጋ እና የተለያዩ አሸባሪ ኃይሎች የሚንቀሳቀሱበት ነው። በመሆኑም የዓለም ኃያላን ሀገራት የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት፣ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር መስራት እና ለባህር በር ጥያቄዋ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት እነዚህን ቀጣናዊ ስጋቶች ለመቆጣጠር ወሳኝ መሆኑን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገነዘቡት መጥተዋል። የተለያዩ ሀገራትም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘትና የደህንነት ስጋቶችን ለመቅረፍ ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ መስራትን እየተረዱ መጥተዋል። በቅርብ ጊዜ ኢትዮጵያ በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ግንኙነት አብሮ ለመስራት እያደረገቻቸው ያሉ ስምምነቶችም ይህንን እንደሚያሳዩ የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ ያሳያሉ፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም መከበር ላይ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ወገኖች፣ ሀገሪቱ የምታነሳው የባሕር በር ጥያቄ በቀጣናው ግጭት እንደሚቀሰቅስ እና ኢ-ፍትሐዊ እንደሆነ በማስመሰል ዲፕሎማሲያዊ ጫና ለማሳደር እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ አካሄድ የቀጣናውን የንግድና የኢኮኖሚ ትስስር የሚያጠናክር እንጂ ግጭትን የሚጋብዝ አለመሆኑንና በአሁኑ ወቅትም ሀገሪቱ እያደረገችው ያለው ጥረት ይህንኑ የሚያረጋግጥ እንደሆነም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

# ትውልድ ተሻጋሪ ልማት



ፎቶ፦ ከፋይል
የፒያሳ የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

**በስንታየሁ ምትኩ**

ከአራት ኪሎ ወደ አምስት ኪሎ በእግር እየተጓዙ ያገኘናቸው አቶ አካሉ በቀለ፣ የአዲስ አበባን የትናንት እና የዛሬ ገጽታ ከሚያውቁ የከተማዋ ነዋሪዎች መካከል ናቸው። በአሁኑ ወቅት መኖሪያቸውን በተለምዶ የካ አባዶ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ሲሆን ከ20 ዓመታት በላይ ፒያሳ ኖረዋል።

"እንደ አሁኑ አካባቢውም ሆነ ከተማዋ ውብ፣ ፅዱና ለኑሮ ምቹ ይሆናሉ ብዬ በጭራሽ አልጠበቅኩም ነበር" የሚሉት አቶ አካሉ፣ ነገር ግን ፕሮጀክቱ እየተጠናቀቀ ሲመጣ የተመለከቱት ነገር ከጠበቁት በላይ ሆኖ አግኝተውታል። ስራው አዲስ አበባን መልክ ከመቀየር አልፎ፣ የሚቀጥለውን ትውልድ ተስፋና ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እርምጃ መሆኑን ነግረውናል፡፡

"አዲስ አበባ ድሮ የነበራት ገፅታ ከአሁኑ ጋር ጭራሽ አይገናኝም፡፡ ከዚህ ይልቅ በፅዳት ጉድለት የምትታወቅና የምትወቀስ ከተማ ነበረች። እኔ ረጅም ዘመን በኖርኩበት ፒያሳ በርካታ ቤቶች ደሳሳ፣ የዘመሙ፣ ለአደጋ የተጋለጡና የተጎሳቆሉ ነበሩ። በተጨማሪም በርካታ ማህበራዊና አካባቢያዊ ችግሮች ነበሩ። አሁን ግን እነዚያ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በሙሉ ተወግደው አካባቢው ፅዱና ውብ ሆኖ አዲስ መልክ ይዟል" ሲሉ የቀደመውንና የአሁኑን በማነጻጸር ይገልፃሉ።

አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ዋና ጽህፈት ቤት መቀመጫ እና የዓለማችን ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት። ከተማዋ የበርካታ ሀገራት ዲፕሎማቶች መኖሪያና የዓለም አቀፍ ስብሰባዎች መድረክ እንደመሆኗ መጠን፤ የከተማዋ ፅዳትና ውበት፣ የምትሰጣቸው አገልግሎቶች እንዲሁም አጠቃላይ ገፅታዋ ይህንኑ ደረጃዋን የሚመጥን ሊሆን እንደሚገባ የሚያነሱት አቶ አካሉ፣ በኮሪደር ልማት የመጣው በጎ ለውጥ፣ ወደኋላ ሳይል ተጠናክሮ ወደ ሌሎች የከተማዋ አካባቢዎችም መስፋፋት እንዳለበት ተናግረዋል።

በአዲሷ ካዛንቺስ የቀን ተቀን እንቅስቃሴያቸውን ከሚያደርጉ ሰዎች መካከል አቶ ማርቆስ ዘበነ አንዱ ናቸው። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ነዋሪ ናቸው፡፡ የሥራ ቦታቸው ካዛንቺስ በሚገኘው በተለምዶ "ጠማማ ፎቅ" ተብሎ በሚጠራው ህንፃ ላይ ነው፡፡ "የቀደመው መንገድ እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ እግረኛና ተሽከርካሪ ተጋፍተው ለመጓዝ ይገደዱ ነበር፡፡ የተቆፋፈረውና ያልተስተካከለው የእግረኛ መንገድ በተለይም አካል ጉዳተኞችን ለከፋ አደጋ ያጋልጣቸው ነበር፡፡ አሁን ላይ ያ ችግርና ስጋት በኮሪደር ልማት ተቀይሯል። እግረኞች በነፃነት የሚያልፉበት ሰፊ የተሽከርካሪ፣ የእግረኛና የሁለት እግር ተሽከርካሪ (ሳይክል) መንገድ ተዘጋጅቷል። በመንገድ ዳር የተዘጋጁት አረንጓዴ ስፍራዎችም ለአካባቢው የተለየ ውበት ከመስጠታቸውም በላይ ነዋሪዎች ንጹህ አየር እየተነፈሱ እንዲንቀሳቀሱና እንዲዝናኑ ዕድል ፈጥረዋል። መንገዶች በመስፋታቸውና አዳዲስ አማራጭ መስመሮች በመገንባታቸው የከተማዋን የትራፊክ መጨናነቅ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል" ሲሉ ትዝብታቸውን ጭምር ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ነዋሪ አቶ በቀለ ኡርጌሳ ናቸው፡፡ ባለፉት ስድስት ዓመታት በሥራ ምክንያት ከከተማዋ ርቀው መቆየታቸውን በመግለጽ፣ በአራት ኪሎና ሜክሲኮ አካባቢዎች የተመለከቷቸው የልማት ስራዎች ግርምትን እንደፈጠሩባቸው አብራርተዋል፡፡ "አንዳንድ አካባቢዎች ጭራሽ የማላውቃቸው እስከሚመስለኝ ድረስ ሙሉ በሙሉ ተለውጠዋል። በእግረኛ መንገዶች ላይ ለዕረፍት የሚሆኑ ማረፊያ ወንበሮች ተተክለዋል፤ ዓይንን የሚስቡና በጣም ፅዱ የሆኑ መንገዶች ተገንብተዋል። ይህ በእውነት እጅግ ደስ ያሰኛል" ብለዋል።

ቀደም ሲል በእግር ለመጓዝ የማይመቹ፣ የቆሻሻ መጣያና የመጥፎ ሽታ ምንጭ እንዲሁም ለደህንነት ስጋት ይደቅኑ የነበሩ አካባቢዎች ዛሬ ፅዱ፣ ውብና በአረንጓዴ ዕፅዋት የተዋቡ መሆናቸውን የገለጹት አቶ በቀለ፣ የኮሪደር ልማት ሥራው ተጠናክሮ ወደ ሌሎች የከተማዋ አካባቢዎች መዳረስ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማ አስተዳደሩ የቀጣይ አምስት ዓመት እና የ2019 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ከሁለት ሳምንት በፊት ውይይት በተደረገበት ወቅት፤ በከተማዋ በዘንድሮ እና በቀጣይ ዓመታት የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የከተማ ማደስ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔም ነሐሴ 2018 ዓ.ም ባደረገው 6ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ በከፊል በኮሪደር ለምተው፣ በከፊል ሳይለሙ የቆዩ አካባቢዎችን በተሟላ ሁኔታ ለማልማት ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል፡፡

ከንቲባ አዳነች በንግግራቸው፣ "በከተማዋ የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች ከአጭር ጊዜ አንጻር የህዝብን ፍላጎት የሚመልሱ ሲሆኑ በረጅም ጊዜ ደግሞ ለትውልድ የሚሻገሩ ሆነው እየተገነቡ ይገኛሉ" ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂና ቢዩልት ኢንቫይሮመንት ኮሌጅ የከተማ ፕላኒንግ መምህርና ተመራማሪ ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካውያን መዲና እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት። ነገር ግን የነበራት የከተሜነት ገፅታ እንዲሁም የምታቀርበው አገልግሎት ስሟንና ሚናዋን የሚመጥን አልነበረም። ከዚህ ቀደም የነበሯት መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ የአረንጓዴ ሽፋን፣ የመንገድ መብራቶች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች እንዲሁም የፍሳሽ፣ ኤሌክትሪክ መስመሮች ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የሚያሟሉ አልነበሩም። አዲስ አበባን ጨምሮ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ከተሞች አመሰራረታቸው ፕላንን መሰረት ያደረገ አልነበረም። ቤቶቹ ወጥነት በሌለው መልኩ ከመሰራታቸው ባለፈ ከፍተኛ የመሬት ብክነትና ኢ-ፍትሃዊ የመሬት አጠቃቀም የሚታይባቸው ናቸው። በነባር ሰፈሮች የነበሩ በርካታ መኖሪያዎች "ቤት" ተብለው ለመጠራትና ለመኖሪያነት የማይመጥኑ እንዲሁ የቤቶች ስብስብ ነበሩ፡፡

የኮሪደር ልማት ሁሉንም ያቀፈና ዘመናዊ የከተማ ልማት ሞዴል መሆኑን የጠቀሱት ብርሃኑ (ዶ/ር)፣ ልማቱ የአዲስ አበባን ገጽታ በመቀየር፤ ከተማዋ ለነዋሪዎችም ሆነ ለቱሪስቶች ምቹ እንድትሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኮሪደር ልማቱ የቆሻሻ መጣያ የነበሩ ቦታዎች ወደ አገልግሎት እንዲገቡ አድርጓል። አካባቢዎቹ ንፁህ፣ ውብና አረንጓዴ በመሆናቸው የመሬት ዋጋ (Land Value) ከፍ እንዲልና ለኢንቨስትመንት ተመራጭ እንዲሆኑም አስችሏል ብለዋል።

ሌላኛው ጥቅም ቀደም ሲል የነበሩ መንገዶች ጠባብና ተሽከርካሪን ብቻ ታሳቢ ያደረጉ ነበሩ። አሁን ግን መንገዶች ከመስፋታቸው ባሻገር ምቹ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች በመሰራታቸው፣ ነዋሪዎች ለአጫጭር ጉዞዎች ታክሲ ከመጠቀም ይልቅ በእግራቸው የመንቀሳቀስ ባህል አዳብረዋል። በዚህም በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ጤናቸውን የሚጠብቁበት ሁኔታ መፍጠሩን ብርሃኑ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

በኢኮኖሚ ረገድም የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባ ቀን ብቻ ሳይሆን ሌሊትም የሚሰራባት ንቁ ከተማ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ በመንገዶች ላይ የሚከልሉ ነገሮች የሉም፤ የደህንነት ካሜራዎች በመገጠማቸው የንግድና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ሌሊትም እንዲሰሩ እድል ፈጥሯል። ዛሬ እነዚህ አካባቢዎች የመዝናኛና የንግድ ማዕከል በመሆናቸው ነዋሪዎችንም ሆነ ቱሪስቶችን የሚስቡ ሆነዋል።

ብርሃኑ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኮሪደር ልማቱ የተገኘው ውጤት፣ የአዲስ አበባን ሁለንተናዊ ገፅታ የቀየረ፤ "እስካሁን የት ነበርን?" ብለን እንድንቆጭ የሚያደርግ በመሆኑ ስራው ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ያልለሙ አካባቢዎችን በመለየት ልማቱን ወደ ሁሉም አካባቢዎች ማዳረስ ያስፈልጋል። ይህንን ዘላቂ የኢኮኖሚና አካባቢያዊ ጥቅም የሚያስገኝ፣ የስራ ዕድል የሚፈጥር፣ ቱሪዝምን የሚያሳድግ፣ የከተማዋን ገፅታ የሚቀይር ልማት ማስቀጠል የመንግስት የቤት ስራ ብቻ አይደለም። እያንዳንዱ ዜጋና ባለሀብት ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለሚመጣው ትውልድ የሚተርፍ ስራ መሆኑን በመገንዘብ በእውቀት፣ በገንዘብና በጉልበት መደገፍና ለውጤታማነቱ መረባረብ አለባቸው፡፡

ከሰሞኑ አዲስ በተመሰረተው የአዲስ አበባ ምክር ቤት በከንቲባነት የተሰየሙት አዳነች አቤቤ በቀጣይ አምስት ዓመታት ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸውን ስራዎች ዘርዝረዋል፡፡ ከነዚህ መካከል የአረጁና የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን ማደስ አንዱ ሲሆን፣ ይህ የስራውን ቀጣይነት በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

## የመዲናዋ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለኮንፈረንስ ቱሪዝም አቅም ከሆኑት መካከል የዓድዋ ድል መታሰቢያ እና የአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል

የአፍሪካ ኅብረት (AU) እና የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (UNECA) ጨምሮ የበርካታ አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ የሆነችው፤ የአህጉሩ የፖለቲካና የኮንፈረንስ ዋና መዲና ተብላ የምትጠራው አዲስ አበባ ከዝርዝሩ ውስጥ አትታጣም፡፡

ዓለም አቀፍ የኮንግሬስና ኮንፈረንስ ማኅበር የከተሞችን የኮንፈረንስ ቱሪዝም ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን በተመለከተ የተለያዩ ሪፖርቶችን፣ የጥናት ውጤቶችንና ተያያዥ መረጃዎችን ይፋ በማድረግ ይታወቃል፡፡ ይህ ተቋም እ.ኤ.አ. 2024/2025 ይፋ ባደረገው ሪፖርት፣ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም እጅግ ከፍተኛ ጥቅም ያገኙ የዓለም ሀገራትን ከተሞች በአሃዛዊ መረጃ አስደግፎ አቅርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት፡- ሊዝበን (ፖርቱጋል) 188፣ ፓሪስ (ፈረንሳይ) 174፣ ባርሴሎና (ስፔን) 166፣ ቪየና (ኦስትሪያ) 159 የሚደርሱ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን በዓመት በማዘጋጀት ቀዳሚ ሆነዋል፡፡

በተመሳሳይ፤ የማህበሩ ሪፖርት የአፍሪካ ሀገራት ከተሞችን ደረጃም በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ አዲስ አበባ ከቀዳሚዎቹ መካከል ተካታለች፡፡ እንደ ሪፖርቱ ከሆነ፡- የደቡብ አፍሪካ ከተሞች (ኬፕታውን እና ጆሃንስበርግ) ባላቸው ዘመናዊ የኮንቬንሽን ማዕከላትና ዓለም አቀፍ ሆቴሎች አማካኝነት በአፍሪካ ቀዳሚ ተጠቃሚ ከተሞች ለመሆን ችለዋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም (UNEP) መቀመጫዋ ናይሮቢ (ኬንያ) በርካታ አህጉራዊ ስብሰባዎችን የማስተናገድ ዕድሉን አግኝታለች፡፡

### የአዲስ አበባ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ዕድሎች

በዓለም ላይ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከል ለመሆን በርካታ ዕድልና ጸጋዎች ከታደሉ ከተሞች መካከል የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ አንዷ ስለመሆኗ ብዙዎች ይስማማሉ። የመዲናዋን እምቅ አቅምን አንድ ሁለት በማለትም ይዘረዝራሉ፡፡ "ዕድሏን ምን ያክል ተጠቀመችበት፣ ምን ምን ሥራዎችን አከናውና ምን መሻሻል አሳየች፣ ምን ጎደላት፣ ለወደፊቱ ምን ታከናውን?" ለሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎች ሙያዊ አስተያየትና ማብራሪያ የሚሰጡ ኢትዮጵያዊያንም ብዙ ናቸው፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም የአዲስ አበባን የኮንፈረንስ ቱሪዝም ተጠቃሚነት በተመለከተ ከጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸውን ሙያተኞችና ምሁራን አነጋግሯል፡፡

አቶ አሸናፊ ካሣ ይባላሉ፡፡ አስጎብኚ ባለሙያ እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ አማካሪ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚናገሩት፣ አዲስ አበባ በብዙ መመዘኛና ምክንያቶች ስትመዘን፣ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከልነት የመመረጥ ዕድልና ጸጋ ካላቸው የዓለም ከተሞች መከካል ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትገኝ ናት፡፡ ይህንንም ትልቅ ጸጋ ያገኘችው በተፈጥሮ፣ በተቋማት ግንባታ፣ በዲፕሎማሲያዊ፣ መንግስት ለኮንፈረንስ ቱሪዝም የሰጠው ትኩረት ከፍተኛነት የመነጨ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

አቶ አሸናፊ አዲስ አበባ ያላትን የኮንፈረንስ ቱሪዝም እምቅ አቅም ሲያብራሩ፤ "ከተማዋ የምትገኝበት መልክዓምድራዊ አቀማመጥ የምድር ማዕከል (እምብርት) የሚባል አካባቢ ላይ ነው፡፡ ይህም ከእስያ እና ከሰሜን አሜሪካ በአማካይ ርቀት እንዲሁም ከአውሮፓ እና ከመካከለኛው ምስራቅ አገራት ደግሞ በቅርብ ርቀት ላይ እንድትገኝ አድርጓታል፡፡ ወደ ከተማዋ መምጣት የሚፈልግ ሰው ከየትኛውም የዓለም አቅጣጫ ተነስቶ በአየር ትራንስፖርት በመጓዝ በአንጻራዊነት በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ ይችላል" ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ፤ "ከተማዋ ያላት የአየር ጠባይ በጣም ተስማሚ የሚባል ነው። ያለአንዳች የቴክኖሎጂ መሣሪያ እገዛ በተፈጥሯዊ የአየር ንብረቷ ከየትኛውም የዓለም ክፍል ለሚመጣ እንግዳ በጣም የተስማማች ነች፡፡ እጅግ ከቀዘቀዘ (በረዷማ) ወይም እጅግ ከሚሞቅ (በረሃማ) አካባቢዎች የሚመጡ እንግዶች በአዲስ አበባ የአየር ንብረት ሲደነቁ መመልከት የተለመደ ነው፡፡ አንዳንዴም ፈጣሪ ለአዲስ አበባ እና ለኢትዮጵያ አድልቷል እስከማለት ይደርሳሉ" በማለት ለአዲስ አበባ ተፈጥሮ የቸራትን ጸጋ መስክረዋል፡፡

> **ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የኮንፈረንስ ማዕከላትን ለአገልግሎት በማብቃት ረገድ፤ ከተማዋ በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ ላይ መሆኗን የሚያሳዩ ተጨባጭ ውጤቶች ብዙ ናቸው**

አዲስ አበባን ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ ልማትና ተጠቃሚነት አቅም የሚሆን ዕድልና ጸጋ የተላበሰች ስለመሆኗ የሚስማሙት የቱሪዝም ከፍተኛ ባለሙያ፣ ተመራማሪ፣ ጸሐፊና መምህር አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አዲስ አበባ ከቀዳሚዎቹ ሦስት የዲፕሎማቲክ እና የዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ ከተሞች አንዷ መሆኗ፣ ስመ ጥሩ እና የስታር አሊያንስ አባል አየር መንገዶች መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም አቅም የሚሆኑ የኮንፈረንስ ማዕከላትን ለአገልግሎት ማብቃቷ... የመሳሰሉት ለከተማዋ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ዕድገት መስፈንጠሪያ እርካቦች መሆናቸውን ዘርዝረዋል፡፡

አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) እንዳብራሩት፤ አዲስ አበባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የአፍሪካ ህብረት፣ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የበርካታ ሃገራት ኢንባሲዎች መቀመጫ በመሆኗ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም የመጠቀም እድል አላት፡፡ ከ110 በላይ ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች ያሉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ መዲናዋ የሚመጡ እንግዶችን ቀልጣፋ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፡፡

በተጨማሪም፤ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም አቅም የሚሆኑ በርካታ ማዕከላት አሏት፡፡ እነዚህ ማዕከላት፡- ቀደም ሲል የነበሩ፣ ዘመኑን በሚመጥን መልኩ የተሻሻሉ እንዲሁም አዳዲስ ተገንብተው ለአገልግሎት የበቁ ናቸው፡፡ ይህም በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ በሺዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎችን ማስተናገድ አስችሏል፡፡ በአንድ ጊዜ፣ በተለያየ ቦታ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን፣ ጉባኤዎችን፣ ስብሰባዎችንና ሁነቶችን ማሰናዳት እና ማስተናገድ የሚቻልበት አቅም ተፈጥሯል፡፡

ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የኮንፈረንስ ማዕከላትን ለአገልግሎት በማብቃት ረገድ፤ ከተማዋ በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ ላይ መሆኗን የሚያሳዩ ተጨባጭ ውጤቶች ብዙ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩትን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስብሰባ ማዕከል፣ የአፍሪካ ህብረት የስብሰባ አዳራሽ፣ መጠናቸው የተለያየ የሆኑ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የጉባኤ ማዕካላት ያላቸው ከ100 በላይ ባለ ኮከብ ሆቴሎች በአዲስ አበባ መገኘታቸው ሳይበቃ፤ ይሄንን በመጠንም ሆነ በጥራት ከፍ የሚያደርጉ አዳዲስ የኮንቬንሽን ማዕከላት ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል። ለአብነት፡- የአዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ማዕከልን፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የኮንፈረንስ ቱሪዝምን ለማሳደግ በከተማ አስተዳደር ደረጃ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የማይስ ቱሪዝም ቡድን መሪ አቶ ለማ ፍቅሬ ገልጸዋል፡፡ በመዲናዋ ያሉ ነባር የቱሪስት መዳረሻዎችን የማሻሻል፣ አዳዲሶችን የመገንባት (የማልማት)፣ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም የሚሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ መዝናኛ ሥፍራዎች፣ የትራንፖርት አቅራቢዎች፣ አስጎብኚዎች...) ደረጃውን የጠበቀና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና የመደገፍ ስራ መከናወኑ ለዘርፉ ተስፋ ሰጪ ውጤት መታየት የበኩሉን ድርሻ መጫወቱን አንስተዋል፡፡

የእንጦጦ እና አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም መገንባታቸው የመጡ እንግዶች በከተማዋ የሚቆዩበትን ጊዜ እና የሚያወጡትን ወጪ ከፍ አድርገውታል። የመስቀል ደመራ፣ የኢሬቻ፣ የኢድ እና ሌሎችም ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ሁነቶች መከናወናቸው፤ የተለያዩ ሙዚየሞች (የአዲስ አበባ ሙዚየም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፣ ኢትኖግራፊክ ሙዚየም...)

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የኪነ ጥበብ መሰናዶዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የመጽሐፍ ምርቃት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

የመምህርና ደራሲ መሰረት አበጀ "ለምሳሌ" መጽሐፍ ዛሬ ቅዳሜ ይመረቃል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለዓመታት ሥነ ጽሑፍ ያስተማረው መምህር መሰረት፣ በተለያዩ መድረኮች የመጻሕፍት ዳሰሳዎችና ሂሶችን በማቅረብ ይታወቃል፡፡ የመጀመሪያ መጽሐፉ የሆነው "ለምሳሌ" የተሰኘው አዲሱ መጽሐፍ የአማርኛ ቋንቋ ውበት፣ የቃላት ጥልቀትና የሥነ ጽሑፍ ክህሎት ጎልቶ የሚታይበት ድርሰት ነው ተብሏል፡፡ በዚህ የመጽሐፍ ምርቃት መርሃ-ግብር ታዋቂ ደራሲያን እና የጥበብ ሰዎች በመጽሐፉ ዙርያ ዕይታቸውን ያጋራሉ፡፡ በዚህ የሥነ ጽሑፍ ማዕድ ላይ የጥበብ አፍቃሪያን እንድትታደሙ በአክብሮት ተጋብዛችኋል። ዛሬ ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ጀምሮ የመጽሐፉ የምረቃ መርሃ ግብር ይካሄዳል፡፡ መጽሐፉ የሚመረቀው ብሔራዊ በሚገኘው በወመዘክር ቤተ መጻሕፍት ብላቴን ጌታ ህሩይ አዳራሽ ውስጥ ነው ተብሏል፡፡

ዛሬ የመጽሐፍ ፊርማ ሥነ ስርዓት ይደረጋል፡፡ በግጥም ሥራዎቿ የምትታወቀው ገጣሚ ምልዕቲ ኪሮስ፣ በቅርቡ ለንባብ ያበቃችው "ጽምፀ ቃል" የተሰኘው የግጥም መጽሐፏ ዛሬ የፊርማ ሥነ ሥርዓት ለገሃር በሚገኘው ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር ይደረጋል፡፡ መርሃ ግብሩ 8:00 ሰዓት የሚጀምር ሲሆን እስከ 10:00 ሰዓት ድረስ ይቆያል ተብሏል።

የጥበብ አፍቃሪያን በመርሃ ግብሩ ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል፡፡

የአንጋፋው ደራሲና ተርጓሚ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ድርሰቶች የሆኑት "የጆካ" እና "አፈርሳታ" የተሰኙ ሁለት መጻሕፍት በአንድነት ታትመው ለንባብ ሊበቁ ነው፡፡ የደራሲ ሣህለ ሥላሴ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ደራሲ ዘነበ ወላ በማህበራዊ የትስስር ገጹ ባጋራው መረጃ፣ "ማተሚያ ቤቱ ሥራዎቹን በፈለግነው ጥራት እና ብዛት አትሞ ማጠናቀቁን አሳውቆናል። እነዚህ መጻሕፍት በቅድሚያ ክፍያ በመግዛት የተባበራችሁትን ወገኖች እያመሰገንን መጻሕፍቱ የሚመረቅበትን ቀንና የጋሼ ሣህለ ሥላሴ 91ኛ ልደት የምናከብርበትን ስፍራ በቅርብ እናሳውቃለን" ብሏል፡፡ በቅርቡ በሁሉም የመጻሕፍት መደብሮች የአንጋፋው ደራሲ መጻሕፎች ለአንባብያን እንደሚቀርቡም አሳውቋል፡፡

## ሥዕል

በኢሬቻ እሴቶች ዙሪያ የሚያጠነጥነው የሥዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ ባለፈው ሳምንት በይፋ የተከፈተው የኢሬቻ የሥዕል አውደ ርዕይ ዛሬን ጨምሮ ለቀጣይ አንድ ሳምንት ለዕይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የሥዕል አውደ ርዕዩ ለገሃር ስቴዲየም አካባቢ በሚገኘው የኦሮሚያ ባህል ማዕከል ውስጥ እየታየ ይገኛል፡፡ መላው የጥበብ አፍቃሪያን በስፍራው ተገኝታችሁ የሥዕል አውደ ርዕዩን እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡

በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴስ በይፋ የተከፈተው የሥዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ ሠዓሊ ሙሉ ለገሰ "I Carry – Je Porte" በሚል ርዕስ በተለያዩ ጊዜያት የሳለቻቸው የሥዕል ሥራዎች የቀረቡበት ይሄ አውደ ርዕይ፣ ባሳለፍነው ሳምንት ሐሙስ በይፋ ተከፍቶ በመታየት ላይ ነው፡፡ ሠዓሊዋ ረቂቅ የአሳሳል ዘይቤ በመጠቀም የሳለቻቸው የጥበብ ሥራዎች እስከ ፊታችን ጥቅምት 21 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ ለዕይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የጥበብ አፍቃሪያንም በሥፍራው ተገኝታችሁ እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡




በመዲናዋ በሳምንቱ ከሚካሄዱ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7:30 ሰዓት "12ቱ እንግዶች" እንዲሁም በ11:30 ሰዓት "በር የሌለው ቤት" ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ እሁድ ደግሞ በ7:30 ሰዓት "ንጉስ አርማሕ" እንዲሁም በ11:30 ሰዓት ደግሞ "እምዬ ብረቷ" ይታያሉ። ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጂ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ "እሳት ወይ አበባ" ዘወትር ቅዳሜ በ11:00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ" ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4:00 ሰዓት "የንባብ ከተማ" የተሰኘው አዲስ የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8:00 ሰዓት "ወህኒ አምባ ቴአትር" እንዲሁም 11:30 ሰዓት ደግሞ "አትጥሪኝ" የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11:00 ሰዓት "አሉ" የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11:30 ሰዓት "ነገሩ አይቆምም"፣ እሁድ በ8:00 ሰዓት "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12:00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ሶስት ማዕዘኑ ላይ በአጠቃላይ ስድስት ቁጥሮች አሉ፡፡ የመሀከለኛውን ቁጥር ትተን በቀኝ መስመር በኩል ወደ ታች የተደረደሩት ሶስቱ ቁጥሮችን መጀመሪያ እናባዛለን። ከዚያ በግራ በኩል ባለው መስመር ላይ የቀሩት ሁለቱን ቁጥሮች ለብቻቸው እንደምራለን፡፡ ከዚያ በኋላ በቀኝ በኩል ያባዛናቸው ሶስቱ ቁጥሮች ድምር ውጤት እና በግራ በኩል ሁለቱ ቁጥሮች ደምረን ካገኘነው ድምር ውጤት ጋር እናካፍላለን፡፡ በዚህ መሰረት ያገኘነው ውጤት የመሀልኛው ቁጥር መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል የመሀልኛው ቁጥር መልስ እንዴት ማግኘት ይቻላል የሚለውን ነው የምንመልሰው፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያውን ሶስት ማዕዘን መልስ አብረን እንስራ፤




5 x 6 x 7 = 210 ይሆናል፡፡ 3 + 7 = 10 ይሆናል፡፡ 210 ÷ 10 = 21 ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፤ 6 x 1 x 9 = 54 ይሆናል፡፡ 4 + 5 = 9 ይሆናል፡፡ 54 ÷ 9 = 6 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ **6** ይሆናል፡፡

## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የማይዳሰሱ ቅርሶች ህያውነት በአዲስ አበባ

**በአብርሃም ገብሬ**

አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ እና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማዕከል ብቻ ሳትሆን፣ የመላው ኢትዮጵያዊያን ባህል እና እሴት ተሰናኝቶ የሚበለጽግባት ትንሿ ኢትዮጵያ ናት። የማይዳሰሱ የተለያዩ አገር በቀል ባህሎች (Intangible Cultural Heritage) በትውልድ ቅብብሎሽ ተጠብቀው እንዲቆዩና ከዘመኑ ጋር ተሰናስለው እንዲያድጉ የከተማዋ አበርክቶ የጎላ ነው። ከአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘናት የተሰበሰቡ ባህሎች፣ ወጎች፣ ዜማዎች፣ ጭፈራዎች እና የአኗኗር ዘይቤዎች በአዲስ አበባ ከባቢ ውስጥ አብረው እየኖሩ የከተማዋን ልዩ ማንነት ፈጥረዋል፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ወርሃ ጥቅምት የመጀመሪው ሳምንት በተለያዩ ዝግጅቶች የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የማይዳሰሱ የአገር በቀል ባህሎች (Intangible cultural heritage) ቀን መነሻ በማድረግ አዲስ አበባ ካላት የባህል ብዝሃነት አንጻር ለእነዚህ ባህሎች ማደግ እና የበለጠ እንዲታወቁ በማድረግ ረገድ ያላትን አበርክቶ እንደሚከተለው በጨረፍታ እናስቃኛችኋለን፡፡

የማይዳሰሱ የአገር በቀል ባህሎች በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የሚገለጡ ናቸው። ውዝዋዜዎቻችን፣ ትረካዎቻችን፣ ከዓለም ጋር ያለን ግንኙነት፣ የእጅ ጥበቦቻችን፣ የአመጋገብ ባህሎቻችን፣ ጭፈራዎቻችን፣ የሙዚቃ ስልቶቻችን፣ ወጎቻችን እና በዓላቶቻችን ያለፉት ትውልዶች ብቻ ሳይሆኑ የዛሬው ማንነታችን መሠረቶችም ናቸው። እነዚህ ህያው የማይዳሰሱ ቅርሶች የባህል ብዝሃነታችን ጥንካሬ እና መገለጫዎች ጭምርም ናቸው፡፡ ባህሎችና ወጎች የመደብዘዝ አደጋ በደቀነባቸው በዚህ በዘመነ-ግሎባላይዜሽን፣ እነሱን ማክበርና መንከባከብ የልዩነታችንን ውበት ጥንካሬ ያሳያል፡፡ እነዚህ የማይዳሰሱ አገር በቀል እሴቶች ለወደፊቱ ትውልድም ትርጉም ያላቸው ሆነው እንዲቀጥሉ ከማድረጋቸውም በላይ በህብረተሰቡ መካከል መከባበርንና ሰላምን የመገንባት ታላቅ አቅም አላቸው። ለዚህ ነው፤ የማይዳሰሱ ቅርሶች አስፈላጊነትና ለሰው ልጆች ያላቸውን ከፍተኛ ዋጋ ለማጉላት የዓለም አቀፍ የማይዳሰሱ ባህሎችና ቅርሶች ቀን (International Day of the Intangible Cultural Heritage) በየዓመቱ ወርሃ ጥቅምት የመጀመሪያ ሳምንት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረው።

ኢትዮጵያ ደግሞ በብዝሃ ባህልና እሴት የደመቀች ሀገር ነች፡፡ በርካታ ሀገር በቀል እሴቶች፣ የዜማ ስልቶችና ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ከእነዚህ ሀገር በቀል ዕሴቶች በውስጧ ይገኙባታል፡፡ እነዚህ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ መልከ ብዙ ጥበባዊ እሴቶች የሀገሪቱን የማህበራዊ ህይወት መስተጋብር ከማጠናከራቸውም በላይ ለዘመናዊው የኪነ ጥበብ ዘርፍ ታላቅ የፈጠራ መሰረት በመሆን አገልግለዋል፤ እያገለገሉም ይገኛሉ።





ፎቶ- ከገፀ ድር

አዲስ አበባ በተለያዩ የአደባባይ በዓላት የደመቀች ከተማ ነች

> **የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዜማዎች፣ ጭፈራዎችና የሙዚቃ መሳሪያዎች በአዲስ አበባ የጥበብ መድረኮች ላይ ተዋህደው የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሀብት መሆን ችለዋል**

በኢትዮጵያውያን ዘንድ በአደባባይ በደማቅ ከሚከበሩ በዓላት መካከል መስቀልና ኢሬቻ ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሁለቱም በዓላት የክረምቱን ጭጋግ ተገፍፎ ወደ ብርሃናማዋ መስከረም ሽግግር ከተደረገ በኋላ የሚከበሩ በዓላት ከመሆናቸው አንጻር በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ መዲናችን አዲስ አበባም እነዚህን በዓላት በደማቅ ሁኔታ ታከብራቸዋለች፡፡ በዓላቱ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ሲከበሩ ከሚታዩት መልከ ብዙ ትዕይንቶች ባሻገር ኢትዮጵያውያንን በማስተሳሰርና በማቀራረብ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ከዚህ አንጻር መዲናዋ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህሎች እንዲያድጉ፣ የጋራ እንዲሆኑና ተጠብቀው እንዲቀጥሉ ገንቢ አስተዋጽኦ እያደረገች መሆኗን ያሳያል፡፡ በዓላቱ በአደባባይ ሲከበሩ ኢትዮጵያውያንን ከማስተሳሰርና ከማዝናናት ባሻገር የጋራ ትርክትን በመፍጠር ረገድም አስተዋጿቸው ትልቅ ነው፡፡

ደራሲና ጋዜጠኛ ዋለልኝ አየለ ባለፈው ዓመት ባሳተመው "የብሌን አንዳች" የተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ስለተለያዩ ባህሎች፣ አመጋገቦችና የባህል ቤቶች አስፍሯል፡፡ ይሄን መነሻ አድርገን ስለ መዲናዋ ባህሎችና የባህል ምግብ ቤቶች አስተያየቱን ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አጫውቶናል፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የባህል ምግብ ቤቶች እና ዘመናዊ ሆቴሎች ይላል ደራሲና ጋዜጠኛ ዋለልኝ አየለ፣ የኢትዮጵያን የብዝሃ ባህል እሴቶች እንዲታወቁ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ እነዚህ እሴቶች እንዲታወቁ እና የጋራ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ በተለይ የባህል ምግብ ቤቶች ትልቅ ድርሻ ይይዛሉ። በአንድ ማዕድ ላይ የሚቀርቡት የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህላዊ ምግቦች፣ የምግብ አሰራር ጥበቦች፣ በባህል የሙዚቃ መሳሪያ የታጀቡ ሙዚቃዎችና ጭፈራዎች በኢትዮጵያውያን መካከል የባህል መስተጋብሩ እንዲጎለብት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ብሏል፡፡

እንደ ደራሲ ዋለልኝ አስተያየት፣ ከከተማዋ ውድና ተወዳጅ የባህል ምግቦች መካከል አንዱ ክትፎ ነው። በባህል ምግብ ቤቶች ደጃፍ ላይ "የጉራጌ ክትፎ አለ" ብሎ ባነር መስቀል ትልቅ ገበያ የመሳቢያ ማስታወቂያ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ አዲስ አበቤዎች ክትፎን በባህላዊ አሰራሩና አቀራረቡ ተማርከው ስለሚመገቡት ነው፡፡ ዛሬ ላይ ክትፎ ከኢትዮጵያ ተወዳጅ የባህል ምግቦች አንዱ እንዲሆን አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድ የከተማዋ የባህል ምግብ ቤቶችና ከተማዋ ለዚህ የባህል ብዝሃነት የተመቸች በመሆኗ ምክንያት ነው፡፡ ይህ አይነቱ የባህል መወራረስ ትስስር ሀገራዊ የወል ማንነት ከፍ ከማድረጉም ባሻገር፣ ከተማዋን የባህል ብዝሃነት በተግባር የሚታይባት ተጨባጭ መድረክ እንዳደረጋት አጫውቶናል።

በእርግጥም የተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዜማዎች፣ ጭፈራዎችና የሙዚቃ መሳሪያዎች በአዲስ አበባ የጥበብ መድረኮች ላይ ተዋህደው የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሀብት መሆን ችለዋል። የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከዘመናዊ የሙዚቃ ቅኝቶች ጋር በመዋሃድ የተፈጠረውና ለዓለም አቀፍ ደረጃ የበቃው የኢትዮ-ጃዝ (Ethio-Jazz) ዘውግ የዚህ ጥበባዊ ውህደት ትልቅ ማረጋገጫ ነው። ዛሬ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ የተለያዩ የጃዝ ሙዚቃ የሚጫወቱ የጥበብ መድረኮች አሏት፡፡ በርካታ አዲስ አበቤዎች የጃዝ ሙዚቃ በሚዘጋጅባቸው መድረኮች ላይ ይታደማሉ፡፡ በዚህም አዲስ አበባ የማይዳሰሱ ባህሎችን ጠብቃ ከማቆየት ባለፈ፣ ፈጠራ ታክሎባቸው ለዓለም እንዲተዋወቁ የራሷን አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡

በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በከተማዋ የተገነቡት ዘመናዊ የጥበብ ማዕከላት፣ ቴአትር ቤቶች እና የባህል መድረኮች ለብዝሃ ባህል ማደግ አዲስ ህይወት ዘርተዋል። እነዚህ ማዕከላት የልዩ ልዩ ብሄረሰቦችን ታሪክ፣ ትረካ፣ ውዝዋዜ እና ድራማዊ ጥበቦች በማስተናገድ ረገድ እድል እየፈጠሩ ናቸው። በጥበብ አማካኝነት የማህበረሰቦችን ታሪክ እና እሴት ለህዝብ ማቅረባቸው፣ ባህሎቹ ሳይዘነጉ እንዲቀጥሉ ገንቢ ሚና እየተወጡ ናቸው፡፡

ጥበብን ከባህል ጋር ያሰናኙት የአዲስ አበባን የጥበብ ማዕከላትና መድረኮች፣ መዲናዋ "ትንሿ ኢትዮጵያ" እንድትሆን አድርጓታል። አዲስ አበባ የሁሉም ባህል መኖሪያና የአብሮነት ተምሳሌት በመሆኗ፣ የማይዳሰሱ ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩና እንዲጎለብቱ ምቹ ሁኔታ ፈጥራለች። ህዝቦች እርስ በእርስ የሚተዋወቁበት፣ የሚደጋገፉበትና አብረው የሚያድጉበት ማህበራዊ መሰረት በመሆኑም የከተማዋ ሚና ከፍተኛ ነው።

የቱሪዝም ጉዳዮች ፀሃፊና ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጠው አስተያየት፣ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የባህል ምሽት ቤቶች የቱሪስቶችን ትኩረት በመሳብ የታወቁ ናቸው፡፡ እነዚህ የባህል ምሽት ቤቶች ልብ ብለን ካየናቸው የምሽት ቤቱ ባለቤት ትርፉን ለማሳደግ በሚል ከቢዝነስ አንጻር ነው ጉዳዩን የሚመለከተው፡፡ ነገር ግን እንደ ሀገርም ሆነ እንደከተማ የውጭ ምንዛሬ ከምናገኝባቸው መንገዶች አንዱ ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን እንዲመጡ በማድረግ፣ ከመጡም በኋላ በሚጠቀሟቸው አገልግሎቶችና የሚቆዩበትን የጊዜ ርዝማኔ ማራዘም ሲችሉ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በመዲናዋ የሚገኙ የባህል ምሽት ቤቶች አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆናቸውን ተናግሯል፡፡

በአጠቃላይ አዲስ አበባ ከአፍሪካ መዲናነቷ ባሻገር፣ የአገሪቱን መልከ-ብዙ የማይዳሰሱ ቅርሶችና አገር በቀል እሴቶች አቅፋ በመያዝ ለዓለም የምታስተዋውቅ ትንሿ ኢትዮጵያ ነች፡፡ ከአደባባይ በዓላት እስከ ባህል ምሽት ቤቶች፣ ከክትፎ እስከ ኢትዮ-ጃዝ ያሉ ጥበባዊና ማህበራዊ መስተጋብሮች የከተማዋን ልዩ ማንነት እያጎሉ ሁላችንንም በጋራ ያስተሳሰሩን እሴቶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህን የማይዳሰሱ ቅርሶቻችንን መንከባከብ፣ ማልማትና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡

# ከሰብዓዊ አገልግሎት እስከ ትውልድ ግንባታ

- **የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ትውልድን በመልካም ስነ ምግባር በማነፅ ረገድ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ተገልጿል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በጦርነትና በስደት ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች ሰብዓዊ ድጋፍ የመስጠት አስፈላጊነት በጎላበት ወቅት እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ። በተለይም እ.ኤ.አ በ1863 በሄንሪ ዱናንት አነሳሽነት የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር መመስረት የነጻ አገልግሎት ባህልን በተደራጀ መልኩ ለማስፋፋት መሰረት ጥሏል። የሰው ልጅ ለወገኑ የማሰብ ተፈጥሮአዊ ደመነፍስ በሂደት ተቋማዊ ቅርፅ በመያዝ፣ ዛሬ ላይ ድንበር ሳይገድበው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለችግሮች ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበትና የማህበረሰብ እድገት ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር ለመሆን በቅቷል፡፡

ይህ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተግባር ፋይዳው ከፍተኛ ነው። ከኢኮኖሚ አንጻር የመንግስታትንና የድርጅቶችን ከፍተኛ የሰው ኃይል ወጪ በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ሲሆን፣ በማህበራዊ ህይወት ደግሞ የህዝቦችን አብሮነት፣ እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህልና ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራል። ከዚህም ባሻገር ለሰጪው አካል የውስጥ እርካታን እና የስነ-ልቦና ጥንካሬን በመስጠት ረገድ ያለው ሚና እጅግ የጎላ በመሆኑ፣ የበጎ ፈቃድ ስራ የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫና የታላቅነት ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

በአዲስ አበባ ከተማም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተጠናከረ መጥቷል። አገልግሎቱ በበጋ እና በክረምት ወቅት የሚሰጥ ሲሆን፣ በዘንድሮው የክረምት ወቅትም በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች በተግባር ላይ ተሰማርተዋል፡፡ በተለይ አካባቢን በማጽዳት፣ ደም በመለገስ፣ የአቅመ-ዳከሞችን ቤቶች በማደስ፣ ህፃናትን በማስተማር፣ ረዳት የሌላቸው ታማሚዎችን በመደገፍና በመንከባከብ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ስለማበርከታቸው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አስራት ንጉሴ በተለይ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደገለፁት፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዋናው ዓላማ ማህበረሰቡን መጥቀም እና ችግረኞችን መርዳት ቢሆንም፣ በሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች ለወደፊት የራሳቸውን የህይወት ልምድ የሚቀስሙበት ብቻ ሳይሆን ለስራቸው የሚጠቅም ጠንካራ እና አርኪ የህይወት ልምድ የሚይዙበትም ነው፡፡

እንደ እርሳቸው ገለፃ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ተሳታፊዎችን በስነ-ልቦና፣ በክህሎት እና በማህበራዊ ህይወት አሸናፊ ከማድረጉም ባሻገር ለግል ስኬታቸው ትልቅ መሰረት ይጥላሉ። በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ ምርሃ ግብር ዜጎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአራዳ ክፍለ ከተማ አምስት ኪሎ አካባቢ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የትራፊክ እንቅስቃሴን ሲያስተናብሩ

ማህበራዊ ፍትሕ በከተማዋ ለማረጋገጥ ብሎም ሰብዓዊ ልዕልናን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ 18 የስምሪት መስኮችና 19 ንዑሳን ፕሮግራሞች ወጥተው ሲሰራባቸው ነበር፡፡ ተግባሩ በአንድ በኩል ዜጎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት በሌላ በኩል ደግሞ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች ተጠቃሚ የሆኑበት ነው፡፡

በክረምቱ መርሃ ግብር በዋናነት ከተከናወኑ የበጎ ፈቃድ ስራዎች መካከልም የቤት ግንባታ፣ ማዕድ ማጋራት፣ በአንድ ቤተሰብ አንድ ሰው መርሃ ግብር እንዲሁም የህፃናት ድጋፍና ሌሎች ተግባራት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ይህ አስተዋፅኦ በእውቀት፣ በጉልበት፣ በሙያና በገንዘብ የተደረገ ሲሆን፣ በገንዘብ ሲተመን ወደ 9 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ሃብት እንደሆነም አረጋግጠዋል፡፡

"በጎነት ለአዲስ አበባ ከፍታ" በሚል መሪ ቃል በሰኔ ወር 2018 ዓ.ም የተጀመረው የዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ መርሃ ግብር እስከ መስከረም 30 ቀን 2019 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፣ 9 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሀብት በማሰባሰብ መርሃ ግብሩ እንደተተገበረ አረጋግጠዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የነበሩ አፈጻጸሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መምጣታቸውን ጠቅሰው፣ እንደ ከተማ የተቀመጠው የመጨረሻው ግብም በጎ ፍቃደኝነትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ መገንባት መሆኑንና በየጊዜው በሚደረገው የስራ ተሳትፎ ግምገማም የተሳትፎ ቁጥርና ተጠቃሚነት በእጅጉ እያደገ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡

በክረምት የበጎ ፈቃድ መርሃ ግብር ሃብት የሚያሰባስቡና አገልግሎት የሚሰጡ 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን በጎ ፈቃደኞችን በተለያየ ዘርፍ በማሰማራት 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አመላክተዋል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ አምስት ኪሎ አካባቢ የሚታየው የትራፊክ እንቅስቃሴ በወጣቶች ቅን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳልጦ ይውላል። በራሳቸው ተነሳሽነትና ሙሉ ፈቃደኝነት መንገድ ላይ በመቆም የትራፊክ ፍሰቱን የሚያስተባብሩት እነዚህ ወጣቶች፣ ለህብረተሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ለራሳቸውም ጥልቅ የአዕምሮ እርካታን ያጎናፀፉቸዋል። ወጣት ቡዛየሁ ገረሱ እንደምትናገረው፣ በቅንነት ሰዎችን ማገልገል በሕይወቷ ውስጥ ትልቅ ደስታና ሰላም እንደፈጠረላት ገልጻለች።

በተመሳሳይ ዘርፍ ለረጅም ዓመታት በመሰማራት አርአያ የሆነው የአራዳ ክፍለ ከተማ የበጎ ፈቃድ ማህበር ምክትል አስተባባሪ ብርሃኑ ተካ፣ አገልግሎቱን ከጀመረ ይኸው 15 ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚያው አካባቢ እንቅስቃሴዎችን ሲያስተባብር ያገኘነው ወጣት ብርሃኑ፣ በጎ ፈቃደኝነት ጊዜያዊ ተግባር ሳይሆን ለወደፊቱም የሕይወቱ የማይነጠል አካል አድርጎ እንደሚያስቀጥለው በጽኑ ቁርጠኝነት አረጋግጧል።

በልደታ ክፍለ ከተማ የመንገድ ላይ ትራፊክ የማስተባበር ስራ ሲሰራ ያገኘነው ወጣት ሃብታሙ መኳንንት ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ክረምት በመጣ ቁጥር በተለይ በችግኝ ተከላና የአካባቢ ፅዳት፣ ደም በመለገስ፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስን ጨምሮ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ ስራዎች ላይ እንደሚሳተፍ ገልፆ፣ ይህን ማድረጉ ከፍተኛ የሆነ የስነ-ልቦና እርካታ እና የአዕምሮ ሰላም እንደሚሰጠው ተናግሯል፡፡

ሰዎችን በመርዳት የሚገኝ ውስጣዊ ደስታ በምንም የሚገለፅ አይደለም የሚለው ወጣቱ፣ በተግባሩ ለተሳተፈ አንድ ወጣትም ሆነ ለሌላው ተሳታፊ የሙያ መሠረት የሚጥል፣ የስራ ዓለምን ተወዳዳሪነት እና ውጣ ውረድ አስቀድሞ በልምድ የሚያስጨብጥ ድንቅ የህይወት ትምህርት ቤት እንደሆነም መስክሯል፡፡

የበጎ ፈቃድ ስራዎች የተለያየ አስተሳሰብ፣ ባህሪ እና ዳራ ካላቸው ሰዎች ጋር በጋራ ወይም በቡድን የሚከወን እንደመሆኑ አንዱ ከአንዱ ልምድ የሚቀስምበት ብሎም አዳዲስ ክህሎቶችን ለመቅሰብ ከማስቻሉም በቅንጅት መስራት፣ ችግርን የመፍታት እና የአመራር ብቃትን በተግባር ለመለማመድ ሰፊ እድል እንዳለውም ነው የተናገረው፡፡

አቶ ኃይሌ ማሞ የተባሉ ሌላው የከተማዋ ነዋሪም በጎነት እድሜ፣ ፆታ፣ ቋንቋና እምነት ሳይለይ ለሰዎች መልካም መሆን እንደሆነ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም በዋናነት ለተቸገሩ መርዳትና መፍትሔ መስጠት ቢሆንም፣ በበጎ ፋቃድ ስራዎች የሚሳተፉ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ እርካታን የሚያገኙበትና ወደፊት ለሚገቡበት የስራ ዓለም የሚጠቅም ጠንካራ የህይወት ልምድ የሚያገኙበት ነው ይላሉ፡፡ በአዲስ አበባ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ እየተመራ እያደገና እየተሻሻለ የመጣ ተግባር ቢሆንም በጎነት ከጥንት ጀምሮ የነበረ ዕርስ በዕርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ውጤት ነው ባይ ናቸው፡፡

እሳቸውም በስራ ቦታቸውም ሆነ በመኖሪያ አካባቢያቸው የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በመስጠት እንደሚሳተፉ በቅርቡም መገናኛ አካባቢ በተዘጋጀ የደም ልገሳ ፕሮግራም ደም መለገሳቸውን እንደዚሁም ሌሎች ሰዎችን በማስተባባር ከ1 ሺህ 800 ለሚበልጡ በገጠሪቱ አካባቢ ላሉ የችግረኛ ቤተሰብ ተማሪዎች ደብተር፣ እስክርቢቶና ሌሎች የመማሪያ ቁሶችን ማበርከታቸውን ተናግረዋል፡፡

በበጎ አድራጎት ስራዎች መሳተፍ በተለይ ወጣቶች ሰዎች በመረዳዳት እንጂ በመቀማማት መኖር እንደማይችሉ ይገነዘባሉ፤ በዚያው ልክ ትውልድም መረዳዳትንና መደጋገፍን እየተማረና እያሰበ ከሄደ የሰከነ፣ አገሩንና ወገኑን የሚወድ ትውልድ እየተፈጠረ ይሄዳል። ይህ እሳቤ በትምህርት ቤቶች፣ በወጣት ማዕከላትና ወጣቶች በሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ሁሉ መዳበር እንዳለበት ለዚህ ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ሽፋን ከመስጠት ጀምሮ የተለያዩ የንቅናቄ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስነ ልቦና ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ታምሬ አንዷለም (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የሰው ልጅ የግልና የጋራ ህይወቱን የሚለውጠው ዕርስ በዕርሱ በመተባባር ነው ብለው፣ ሰዎችን ለመርዳት በነፃ በበጎ ፈቃደኝነት የሚከናወኑ ተግባራትም ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበት መስጠትን የሚጠይቁ ሲሆን፣ ይህም የህብረተሰብ የጋራ ለውጥን ያመጣል ብለዋል፡፡

የሰው ልጅ ለሌላው ለውጥ ሲባል በሚሰጠው የህይወት መስዋዕትነት የህሊና እርካታን ከማግኘት ባለፈ ጠቃሚ የህይወት ልምዶችን ይቀስማል፤ በተለይ ደግሞ ተግባሩ በወጣቶች ከተሰራ ሀገራዊ ማህበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣት ይጠቅማል፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳታፊዎች ገንዘብ ባያገኙም ትምህርት፣ እውቀት፣ ክህሎትና ለቀጣይ ህይወታቸው ልምድ ያገኙበታልም ነው ያሉት፡፡

በህይወት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ከሰው ጋር መግባባት፣ አካባቢን ማወቅና ነገሮችን መረዳት ብሎም ለውጥ እንዴት እንደሚመጣ በተግባር ማየትን ይጠይቃል ያሉት መምህሩ፣ ለዚህ ደግሞ የበጎ ፈቃድ አድራጎት ስራዎች የላቀ ድርሻ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

# ልጆች፤ የትምህርት ቤታችሁን ንፅህና እንዴት እየጠበቃችሁ ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፣ የትምህርት ቤት ፅዳት ወይም ንፅህና እንዴት እንደሚጠበቅ፣ ምን አይነት ጥቅም እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ? እናንተስ የትምህርት ቤታችሁን ፅዳት ምን ያህል ትጠብቃላችሁ? በዚህ ጉዳይ ላይ ከጓደኞቻችሁ አልያም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ሃሳብ ተለዋወጡ፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ደግሞ የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ፅዳት የሚጠብቁ ልጆችን ልምድና ተሞክሮ እንደሚከተለው ያካፍላችኋል፡፡ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ፡፡



ፎቶ፡- ከፋይል

የትግል ለነፃነት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ትምህት ቤታቸውን ሲያፀዱ

አባይነሽ ጊጋ እባላለሁ፡፡ የትግል ለነፃነት ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ትምህርት ቤታችን ተፀድቶና ውብ ሆኖ ነው የተቀበለን፡፡ እኛ ተማሪዎች ደግሞ ፅዳቱን ጠብቀን ምቹ እንዲሆን ማድረግ አለብን፡፡ እኔ የትምህርት ቤቴን ንፅህና የምጠብቀው የመጀመሪያው ቆሻሻን የሚበሰብስ፣ የማይበሰብስ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻ ማስወገጃ ተብለው በተቀመጡ ቅርጫቶች ውስጥ በአግባቡ በመጣል ነው፡፡ በሳምንት አርብ አርብ ሁሉም ተማሪ ሲያፀዳ እኔም በመሳተፍ ለፅዳቱ መጠበቅ የበኩሌን አስተዋጽኦ አደርጋለሁ፡፡

የትምህርት ቤቴን ፅዳት ስጠብቅ የመጀመሪያዋ ተጠቃሚ ራሴ ነኝ፡፡ ይህም ማለት በፅዳት ጉድለት ምክንያት ከሚመጡብኝ በሽታዎች ይታደገኛል። አይኔም ንፁህና ፅዱ ቦታ እያየ ነው፡፡ አዕምሮዬም ሰላም ያገኛል፡፡ ትምህርት ቤቴን ወድጄው እንድመጣና ትምህርቴን እንድከታተል አድርጎኛል፡፡

ሮዳስ ዋሴነህ እባላለሁ፡፡ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 10 ዓመቴ ነው፡፡ ፅዳት ለሰው ልጆች ወሳኝ እና አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ፡፡ በዚህም ከግል ንፅህና በመጀመር የትምህርት ቤቴንም ፅዳት እጠብቃለሁ፡፡ ይህንንም አርብ አርብ በሚካሄደው የፅዳት ዘመቻ ላይ በመሳተፍ፣ ወረቀትን ጨምሮ የተለያዩ ነገሮችን ለቆሻሻ መጣያ ተብሎ በተዘጋጀ ቅርጫት ላይ አስቀምጣለሁ፡፡ መፀዳጃ ቤት ስጠቀም ውሃ እደፋለሁ፡፡ ሌሎች ጓደኞቹ ቆሻሻን በየቦታው ሲጥሉ ካየሁ በቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ እንዲያስወግዱ እነግራቸዋለሁ፡፡

የራሴን ንፅህና ጠብቄ የምውልበትን ትምህርት ቤት ማቆሸሽ የተማርኩትን የንፅህና አጠባበቅ ትምህርት በተግባር አላዋልኩትም እንደማለት ነው፡፡ ትምህርት ቤቴ ጽዱ መሆኑ በንጽህና ጉድለት ከሚመጣ በሽታ ጠብቆኛል። ትምህርቴን በአግባቡ እንድከታተል አድርጎኛል፡፡ ትምህርት ቤቱም ውብና ማራኪ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

መቅደስ እንዳወቅ እባላለሁ፤ በትምህርት ቤቱ የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ 11 ዓመቴ ነው። ንፅህና ከራስ ይጀምራል። በዚህም የግል ንጽህናዬን ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ እንደምጠብቅ ሁሉ ከጠዋት እስከ ማታ የምማርበትን ትምህርት ቤት ፅዳት መጠበቅ ግዴታዬ ነው፡፡ ክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጭ ቆሻሻን በየቦታው ባለመጣል ኃላፊነቴን እወጣለሁ፡፡

አርብ አርብ በሚካሄደው የፅዳት ዘመቻ ላይ እሳተፋለሁ፡፡ የከረሜላና ብስኩት ወረቀት፣ የፍራፍሬ ልጣጭ፣ ሃይላንድ የመሳሰለውን ቆሻሻ በአግባቡ የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ አስወግዳለሁ። በግቢው ውስጥ ያሉ አትክልቶች እና ዛፎች ላይ ጉዳት አላደርስም፡፡ ኳስ በምንጫወትበት ሜዳ ላይ ወረቀትም ሆነ ሌላ ነገር አልጥልም። የትምህርት ቤቴን ፅዳት እንድጠብቅ ያደረገኝ በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለ ፅዳት መማሬ እና የትምህርት ቤቱ መምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ቆሻሻን በየቦታው እንዳንጥል በሚያስተላልፉልን መልዕክት አማካኝነት ነው፡፡

የትምህርት ቤቴ ፅዱ መሆን የሚያስገኙልኝ ጥቅሞች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ እንደ ጉንፋን ካሉ ተላላፊ በሽታዎች ይከላከልልኛል፡፡ የትምህርት ቤቱ ውበትም ይጨምራል፤ እይታንም ይማርካል፡፡ ስለዚህ ልጆች የትምህርት ቤታችንን ንጽሕና በጋራ እንጠብቅ፡፡

## የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ



ሰንደቅ ዓላማ የአንድን ነፃ ሀገር ሉዓላዊነት፣ የሕዝቦችን ታሪክ፣ አንድነትና ማንነት የሚወክል ብሔራዊ ዓርማ ነው። ሰንደቅ ዓላማ የሚለው መጠሪያ ከሁለት ቃላቶች የተመሰረተ ነው፡፡ "ሰንደቅ" የሚለው ቃል ምርኩዝ፣ ምሰሶ ወይም በትር ማለት ሲሆን፣ "ዓላማ" ማለት ደግሞ ምልክት ወይም አቋም ማለት ነው፡፡

ሰንደቅ ዓላማ የአገር እና የህዝብ ምልክት በመሆኑም ከሰንደቅ ዓላማው ፊት በቆመ ቁጥር የሀገሩ ምስል የማይከሰትበት ሰው የለም፡፡ ከዓለም ታሪክ እንደምንረዳው ሀገራትና ዜጎች ከቀኝ ግዛት ተፅዕኖ ሲላቀቁ መጀመሪያ ከፍ አድርገው የሚያሳዩት ሰንደቅ አላማቸውን ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ(ኢፌዲሪ) ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 3(2) እና በአዋጁ አንቀፅ 6 መሰረት የሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ቅርፅ ምን መሆን እንዳለበት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሃል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ የተቀረፀ ብሔራዊ ዓርማ አለው። ዓርማው በሰንደቅ ዓላማው መሃከል ላይ የሚያርፈው የክቡ ዙርያ የአረንጓዴውንና የቀዩን ቀለማት ቁመት አጋማሽ አካሎ የሚይዝ መሆን አለበት፡፡ ሦስቱ ቀለማት ደግሞ እኩል ሆነው በአግድም የሚቀመጡ ሲሆን ቀለማቱ ብሩህ፤ ደማቅ የሆኑና ያልተቀላቀሉ መሠረታዊ መሆን አለባቸው፡፡

የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት የየራሳቸው ትርጉም አላቸው፡፡ በአንቀፅ 7 ላይ እንደተገለፀው አረንጓዴው የስራ፣ የልምላሜና የእድገት ምልክት ሲሆን፤ ቢጫው የተስፋ፣ የፍትህና የእኩልነት ምልክት ነው፡፡ ቀዩ ደግሞ ለነፃነትና ለእኩልነት መስፈን የሚደረግ የመስዋትነትና የጀግንነት ምልክት ነው፡፡ ክብ ሰማያዊ መደብ ደግሞ የሀገሪቱን ዘላቂ ሰላም የሚያሳይ ሲሆን፤ ቀጥታና እኩል መስመሮች ያሉት ኮከቡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በመፈቃቀድና በእኩልነት የመሠረቱትን አንድነትን ያመለክታል። የሚፈነጥቀው ቢጫ ጨረር ደግሞ ለሕዝቦች ብሩህ ተስፋና ብስራት ያበስራል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 654/2001 አንቀፅ 4 ላይ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በየዓመቱ መስከረም ወር ሁለተኛው ሳምንት ሰኞ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደሚከበር ደንግጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 863/2006 አማካኝነት በተደረገው የሰንደቅ ዓላማ ማሻሻያ አዋጅ ደግሞ የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በየዓመቱ ጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሰኞ በአገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡

**ምንጭ ፡- የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር**

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እግሩ አንድ ጭንቅላቱ ሦስት**

**መልስ፡-** ሐ.መንሽ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**በትልቅ ምጣድ ትንሽ እንጎቻ ?**

ሀ.ፀሐይ

ለ. ጨረቃ

ሐ.ሰማይ

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የከተማዋ የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት አስተዳደር ስራ እንዴት እየተተገበረ ነው?

**በደረጀ ታደሰ**

በዘመናዊው ዓለም የዲጂታል ቴክኖሎጂ አስፈላጊነት በጣም እያደገ እና ወሳኝ እየሆነ መጥቷል፡፡ ቴክኖሎጂው የሀገራት እና የከተሞች ሁለንተናዊ ዕድገት የስኬታማነት ደረጃን የመወሰን አቅሙ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ ሆኗል። ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና መሰል ገዳዮች ፈጣኑን የዓለም ለውጥ ባገናዘበ መልኩ በውጤታማነት ለማስቀጠልም ተኪ የማይገኝለት ሞተር አድርጎ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ ላይ በስልጣኔያቸው፣ በዘመናዊነታቸው እንዲሁም ለነዋሪዎቻቸው እና ለጎብኚዎቻቸው ምቹ በመሆናቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ ከተሞች፤ "ይህንን ክብርና መመረጥ ያስገኘላቸው ምስጢር ምንድን ነው?" ብለን ከጠየቅን ምላሹ፤ "ከተሞቹ ለስሉጥ ከተማነት (Smart City) ግንባታ ቁልፍ አቅም የሆነውን የዲጂታል ቴክኖሎጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋለቸው ነው፡፡" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የኢትዮጵያ መዲናና የዲፕሎማቲክ ማዕከሏ አዲስ አበባ፤ ወደስሉጥ ከተማነት (Smart City) የሚያሸጋግራትን ሰፊ ርዕይ ሰንቃ ወደ ተግባር ገብታለች፤ በሥራዎቹም አበረታች ውጤት መመዝገባቸው ቀጥለዋል። በዚህ ታላቅ እና ግዙፍ የለውጥ ሂደት ውስጥ ከፌደራል መንግስት ጀምሮ ከተማ አስተዳደሩ እና የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተሳትፈዋል፤ እየተሳተፉም ይገኛሉ። እንደ ከተማ አስተዳደር ካሉ ተቋማት አንጻር ከተመለከትን፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ማዕከላዊውንና ቁልፉን ሚና በመወጣት በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ የከተማዋ ስሉጥ ከተማነት (Smart City) እንዲሳካ እየከወናቸው ካሉ በርካታ ተግባራት መካከል፡- የተቋማትን አስተዳደራዊ አሰራር ማዘመን፣ ለነዋሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረግ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ከብልሹ አሠራርና ከእንግልት የጸዱ እንዲሆኑ ማስቻል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። ለዚህ ወሳኝ ተግባር ስኬታማነት ደግሞ በቢሮው ሥር በዘርፍ በዘርፍ የተደራጁ ተግባራቸውን በተቀናጀና በተሰናሰለ መልኩ የሚከውኑ የሥራ ክፍሎች አስተዋጽኦ የላቀ ነው፡፡ ባለፉት ዕትሞቻችንም የቢሮውን የተወሰኑ የሥራ ክፍሎች ለአብነት፡- የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ ዳይሬክቶሬት የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የኦፕሬሽንና ጥገና ዳይሬክቶሬት የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ያስነበብናችሁ መረጃ ለዚህ ምስክር ነው። በዚህ ዕትማችን ደግሞ፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን የሥራ እንቅስቃሴ እንቃኛለን፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ተቋማትን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማዘመን ሚናውን እየተወጣ ነው

ዳይሬክቶሬቱ፤ የከተማ አስተዳደሩን የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የሶፍትዌርና ሲስተም ልማት ፕሮጀክቶችን የማስተዳደር፣ የመከታተልና ጥራታቸውን የማረጋገጥ ቁልፍ ኃላፊነት እንዲወጣ የተደራጀ ነው፡፡ ክፍሉ ባለፉት የለውጥ ዓመታት ውስጥ እንደ አዲስ አበባ ከተማ ለተመዘገቡ የስሉጥ ከተማነት ስኬቶች የራሱን ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል፤ እየተወጣም ይገኛል፡፡ የክፍሉን ተግባርና ኃላፊነት፣ ይህንን ለመወጣት እያደረገ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ፣ በሥራው ለመዲናዋ ዘመናዊነት ያበረከተው አስተዋጽኦ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡን፣ በቢሮው የፕሮጀክት አስተዳደር ውስጥ የፕሮጀክት ግምገማ እና ዶክመንት ቡድን መሪ አቶ አሻግሬ ሞላ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

"አዲስ አበባን ዘመናዊና ስሉጥ (ስማርት) የማድረግ ጉዞ ተፈጻሚ እየሆነ ያለው፡- ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ባደረገ፣ በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ላይ በተመሰረተ እና የከተማዋን አጠቃላይ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነው" ያሉት አቶ አሻግሬ፤ ይህንንም መሰረት በማድረግ ቢሮው በጥናት የተለዩ ስድስት ዋና ዋና ምሰሶዎች ላይ አተኩሮ እየሠራ ይገኛል። እነዚህ ምሰሶዎች፡- ስማርት ኢኮኖሚ፣ ስማርት ከባቢ፣ ስማርት አስተዳደር፣ ስማርት እንቅስቃሴ፣ ስማርት አኗኗር እንዲሁም ስማርት ነዋሪ መሆናቸውንም ዘርዝረዋል፡፡

አቶ አሻግሬ በማብራሪያቸው፣ በከተማዋ የስሉጥ ከተማነት ጉዞ ውስጥ የሚተገበሩ የኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶች ከሃሳብ ማመንጨት (ከጽንሰት) ጊዜ ጀምሮ ወደ ሙሉ ትግበራ እስኪገቡ ድረስ ባለው ሂደት በቢሮው ሥር የተደራጁ የሥራ ክፍሎች የራሳቸውን የጎላ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። የከተማ አስተዳደሩን የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የመዘርጋት፣ የሶፍትዌርና ሲስተም ልማቶችን የመከታተልና ጥራታቸውን የማረጋገጥ ቁልፍ ሥራዎችን በግንባር ቀደምትነት የማከናወን ኃላፊነት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አክለው እንዳብራሩት፤ ከተማዋ በዘመናዊነት፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተሳሰረች፣ ለነዋሪዎቿ እና ለእንግዶቿ በሁሉም መመዘኛ የተመቸች እንድትሆን ለማድረግ ቢሮው ውስጣዊ እና ውጫዊ አቅሙን በማቀናጀት እየሠራ ይገኛል። የተቋሙ ተልዕኮ አካል በሆነው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማት እና ትግበራ ሂደት ውስጥ ለሚከወኑ ለእያንዳንዳቸው ፕሮጀክቶች ከፍተኛ አጽንኦት ይሰጣል። የዲጂታል ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶች መነሻቸው ከተለያየ ሁኔታ ሲሆን፤ በዋናነት በስማርት ሲቲ ዘርፍ በጥናትና ምርምር ከሚለዩ ፍላጎቶች፣ ከከተማ አስተዳደሩ አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ እቅድ፣ ከየተቋማቱ በደብዳቤ ከሚቀርቡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፍላጎት ጥያቄዎች እንዲሁ ከሀገር አቀፍ "የዲጂታል 2030" ስትራቴጂ ግቦች የሚመነጩ ናቸው።

ከላይ በተጠቀሱት መነሻዎች አማካኝነት ወደ ቢሮው የሚመጡ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማት እና ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ምላሽ ከማግኘታቸው በፊት የሚያልፉበት የራሱ አሠራርና መርህ መኖሩን የጠቆሙት አቶ አሻግሬ፤ ሂደቱንም እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡ ከቢሮው የስማርት ሲቲ ስትራቴጂክ እቅድ፣ ከተቋማት የሚመጡ ጥያቄዎችን በመቀበል በስማርት ሲቲ ዘርፍ በጥናት የተለዩትን የመሰረተ ልማት ዘርፍ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የስራ ክፍል በጥልቀት ይገመግማል፤ ይመረምራል፡፡ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት (Feasibility Study) ይከናወናል። የፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናት ማለት፡- ፕሮጀክቱ ከገንዘብ፣ ከጊዜ፣ ከአስፈላጊነት፣ ከቴክኖሎጂ ተቀያያሪ ባህርይ... አንጻር ያለውን ጠቀሜታ የሚመለከት ሲሆን፤ ይህም በሙያተኞች ይሠራል። የአዋጭነት ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ስለፕሮጀክቱ ቀጣይ አተገባበር ሁኔታ በአመራሩ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውን መሰረት በማድረግ እንዲለሙ ወይም እንዲሠሩ የተመረጡ ፕሮጀክቶች ወደ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ትግበራ ክፍሎች ይመራሉ፡፡ እነዚህ ክፍሎች በፕሮጀክት የተያዙ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን የሚያለሙና ወደ ተግባር የሚለውጡ ናቸው፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ማብራሪያ፤ በውሳኔ ሰጪ አመራር የጸደቀ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፕሮጀክት ወደ መጨረሻው ተጠባቂ ውጤት ለመለወጥ የሚያልፍባቸው ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም ደረጃዎች በዋናነት፡-የዕቅድ፣ የትግበራ፣ የጥራት ቁጥጥር እና የተጠቃሚዎች የአጠቃቀም ፍተሻ እና ማጠናቀቅ ናቸው። በዕቅድ ምዕራፍ (Planning Phase) የፍላጎት ልየታ ይከናወናል፤ ዲዛይን ይዘጋጃል፤ የፍላጎት (የጨረታ) ሰነድ (Solution Document) ተዘጋጅቶ ለአልሚዎች እንዲወዳደሩ ይቀርባል። ፕሮጀክቱ እንዴት፣ በማን ይከናወን የሚለው ጥያቄ በትግበራ ምዕራፍ (Implementation Phase) ምላሽ ያገኛል። ከዚያም በእያንዳንዱ የፕሮጀክት ልማት ትግበራ አፈጻጸም ላይ ጥራትና ቁጥጥር ይከናወናል፡፡ በዚህ ወቅት ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት ልማት የሚውሉ ግብዓቶች ጥራት፣ የሲስተም ተግባራዊነት (Functionality) እና የመሳሰሉት በየደረጃው ይፈተሻሉ። በመጨረሻው የተጠቃሚዎች ፍተሻ እና የማጠናቀቅ ምዕራፍ፤ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥና ቀጣይነት እንዲኖረው የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች ይከናወናሉ።

ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ከተቋማት የሚመጡ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ጥያቄዎች መካከል መመዘኛውን ባለማሟላት ተቀባይነት የማያገኙም አሉ፡፡ ጥያቄዎቹ ተቀባይነት ሳያገኙ የሚቀሩት፤ ቀደም ሲል የጸደቁ ፕሮጀክቶችን ለመለየት የሚያስችለውን በሣይንሳዊ ጥናት ሂደት ውስጥ አልፈው ከተመዘኑ በኋላ ነው፡፡ ተቀባይነት ያላገኙ ጥያቄዎች ከሚወድቁባቸው የተለያዩ መመዘኛዎች መካከል፡- በተቋማት መካከል የሥራ ድግግሞሽ መኖርና ጥያቄው ቀድሞ በሌላ ተቋም ቀርቦ ምላሽ ያገኘ መሆኑ አንዱ ነው፡፡ ተቋማቱ በኪራይ ህንፃዎች ውስጥ እያሉ የጠየቁት ጥያቄ ከፍተኛ በጀት የሚጠይቁ ግዙፍ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን የሚፈልጉ እንዲሁም መሰረተ ልማቶቹን ለመዘርጋት አለመመቸታቸው ሌላው ተቀባይነት ሳያገኝ የሚቀርበት ጉዳይ ነው፡፡ የተቋማት ኃላፊዎች መለዋወጥ የሚያስከትለው የግል ፍላጎት መኖር ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው። የዳይሬክቶሬቱ ዋና ሚናም እነዚህን ያልተጠናቀቁና አዋጭ ያልሆኑ ጥያቄዎች በመቆጣጠር(በመመዘኛው መሰረት ገምግሞ በማስቀረት)፣ የከተማዋን በጀትና ሀብት በጥራቱ ከተረጋገጠ ፕሮጀክት ላይ ብቻ ማዋል እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መዲና፣ የአፍሪካዊያን የጋራ ከተማ፣ የዲፕሎማሲ ማዕከል፣ የብዙ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መገኛ የሆነችው አዲስ አበባ የስሉጥ ከተማነት (Smart City) ርዕይ ዕውን ለማድረግ እየተጓዘችበት ያለው መንገድ ትክክለኛነት ገና ከማለዳው እየታየ ያለው ውጤት ምስክር ነው፡፡ ይህንን ውጤት አጠናክሮ ለማስቀጠል፤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተዘረጉ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችንና ሲስተሞችን በጥንቃቄ መጠበቅና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባቸዋል። በተጨማሪም በየተቋሙ የሚገኙ ባለሙያዎችና አመራሮች የቴክኖሎጂ እውቀታቸውን ዘወትር በማሳደግና ከዘመኑ ዲጂታል አሰራር ጋር በመዋሃድ የከተማዋን የስማርት ሲቲ ግብ ለማሳካት አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።

# በጋራ ጥረት የተዋበች ከተማ

- **የአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን ለውጥ የመጣው በመንግሥት ቁርጠኛ መሪነት እና በሕዝቡ ጠንካራ የባለቤትነት መንፈስ መሆኑ ተጠቁሟል**



ፎቶ- ከፋይል

በኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማቶች ውብ መልክ የተላበሰው የአዲስ አበባ ከተማ ከፊል ገፅታ

**በቶለሳ መብራቴ**

አዲስ አበባ ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ የበርካታ ታሪካዊ ክስተቶች፣ የታላላቅ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች እና የባህል ውህደቶች ማዕከል ሆና ቆይታለች። ይሁን እንጂ ለረጅም ዓመታት "የአፍሪካ መዲና" የሚለው ታላቅ ስሟ እና በውስጧ የነበረው የተዝረከረከ፣ ለጥቁር ጭስና ለቆሻሻ የተጋለጠ እውነታ ዕርስ በዕርሳቸው የሚጋጩ ነበሩ። የከተማዋ ነዋሪዎችም በገዛ ከተማቸው መሳቀቅና ለዘመናት የልማት ቁጭት ውስጥ መኖር ግድ ሆኖባቸው ሰንብተዋል።

ዛሬ ግን ያ ታሪክ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። በአጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ውጫዊና ውስጣዊ መልክዋን እየቀየረች፣ የነዋሪዎቿን አንገት ቀና የሚያደርጉና የዘመናት ቁጭትን የሚወጡ ግዙፍ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን እያስተናገደች ትገኛለች። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር መንግሥት ምሥረታ በተከናወነበት 7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ይህን ሀቅ አመላክተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው፣ ከተሞች የዘመናዊ ከተማ መልክ መያዝ መጀመራቸውን ጠቁመው፣ የአዲስ አበባ ከተማ መልክ መለወጥ እና መሻሻሎች ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በመሳብ በኩል የራሳቸውን ሚና እየተጫወቱ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የኢትዮጵያን የውኃ አጠቃቀም እሳቤ እየቀየሩት መሆኑን አንስተዋል፡፡

የአዲስ አበባን የዛሬ ተጨባጭ ለውጥ በጥልቀት ለመረዳት ወደ ኋላ መለስ ብሎ ታሪኳን ማጤን ያስፈልጋል። ከተማዋ "አዲስ አበባ" በሚል ስያሜ ስትመሠረት፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧና የተፈጥሮ ውበቷ እጅግ ተመራጭ አድርጓት ነበር። ይሁን እንጂ ለበርካታ ዘመናት የቀጠለው የከተማዋ ዕድገት ወጥ የሆነ ማስተር ፕላንን የተከተለ ባለመሆኑ፣ መዲናዋን ወደ ሰፊ መንደርነት ቀይሯት ቆይቷል።

መሠረተ ልማቶች የተቆራረጡ፣ የወንዝ ዳርቻዎች የቆሻሻ ማጠራቀሚያና የደህንነት ስጋት የሆኑባት፣ መንገዶቿ ደግሞ ለሰው ልጅ ክብር የማይመጥኑ ጠባብና ጨለማማ የነበሩባት ከተማ ነበረች። ሕዝቡ በወቅቱ በነበሩ መሪዎች ላይ እምነት በማጣቱ፣ ልማት ማለት ይልቁኑ "ማፈናቀል እና ማግለል" መስሎት እንዲሰጋ አድርጎት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

አሁን ግን በአዲስ አበባ እየታየ ያለው ተጨባጭ እውነታ ሙሉ በሙሉ ሌላ ገጽታ ይዟል። እያንዳንዱ የልማት እርምጃ የሕዝብን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማዕከል ያደረገ ሆኗል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደኅንነት መምህርና ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ የአዲስ አበባን የዘመናት የልማት ቁጭት በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቀየር ረገድ የአሁኑ አስተዳደር ያሳየው የማይናወጥ የፖለቲካ ቁርጠኝነትና ግልጽ ራዕይ ቀዳሚውንና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። አስተዳደሩ ከተማዋን እንደ ስያሜዋ እውነተኛ "አዲስ" እና "አበባ" ለማድረግ ካለው ጽኑ ዓላማ በመነሳት፣ ቀደም ሲል ለዓመታት በቢሮክራሲ የተተበተቡ አሠራሮችን ሙሉ በሙሉ ሰብሮ መውጣት ችሏል።

ይህን ታላቅ ራዕይ ወደ መሬት ለማውረድ የተዘረጋውና ሌሊትን ከቀን የዋጀው የ24/7 ሰዓት ተከታታይ የሥራና የክትትል ባህል ደግሞ የከተማዋን የዕድገት ፍጥነት ወደ ላቀ ምዕራፍ አሸጋግሮታል። መሪዎች በየደረጃው ከቢሮ ወጥተው በየፕሮጀክቶቹ ሳይት ላይ ሌሊትና ቀን በመገኘት የሚያደርጉት ጥብቅ ክትትልና አመራር፣ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች በጥራትና በማይታመን ፍጥነት ተጠናቀው ለሕዝብ ጥቅም እንዲበቁ ያስቻለ እውነተኛ የለውጥ ሞተር ሆኗል።

መምህር ሙሉጌታ (ዶ/ር) በገለጻቸው፤ የአስተዳደሩ መሪዎች ከነዋሪው ጋር የፈጠሩት ቀጥተኛና ግልጽ ግንኙነት አሁን ለመጣው የአዲስ አበባ ለውጥ ትልቁን መሠረት ጥሏል። ይህ በሕዝብና በመንግሥት መካከል የተፈጠረው ጥብቅ መተማመን ነዋሪው እያንዳንዱን የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት "የራሴና የልጆቼ ሀብት" ብሎ እንዲቀበለውና የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው አድርጎታል።

ባለሀብቱ በገንዘቡና በሃብቱ፣ ምሁራንና ባለሙያዎች በእውቀታቸው፣ ወጣቱና አጠቃላይ ማኅበረሰቡ ደግሞ በጉልበታቸው የልማቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ ለመሆን ችለዋል። ይህ የሕዝብና የመንግሥት የተቀናጀ የጋራ ድካም፣ ከተማዋ የዘመናት የልማት ቁጭቷን ተወጥታ ዛሬ የምናየውን አንጸባራቂ ድል እንድታስመዘግብ ያስቻለ እውነተኛ የሕዝብ ትብብር ማሳያ መሆኑን መምህሩ አስረድተዋል።

ቀደም ሲል በብልሹ አሰራር፣ በቢሮክራሲና በማስተር ፕላን ጉድለት ምክንያት ይጓተቱና የከተማዋ የዕድገት ማነቆ ሆነው የቆዩ ፕሮጀክቶች፣ ዛሬ ቦታቸውን ለአዲስና አስደናቂ የአፈጻጸም ፍጥነት ለቀዋል። አሁን በከተማዋ በተዘረጋው አዲስና ዘመናዊ አሠራር፣ እያንዳንዱ የኮሪደርም ሆነ የወንዝ ዳርቻ ልማት በሳይንሳዊና ጥራቱን በጠበቀ ጥናት ላይ የሚመሠረት በመሆኑ፣ ዓመታት ይፈጁ የነበሩ ግዙፍ ሥራዎች በጥቂት ወራት ውስጥ ተጠናቅቀው ለአገልግሎት ዝግጁ መሆን ችለዋል። ይህ በጥናት የሚመራ፣ ፈጣን ውሳኔ አሰጣጥን ያካተተና የክትትል ጥራትን ያረጋገጠ አዲስ አሠራር ከተማዋ የዘመናት የልማት ቁጭቷን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድትወጣና የትግበራ አቅሟን ለዓለም የምታሳይበት ዋነኛ መሣሪያ ሆኗል።

የሰላምና ደህንነት መምህሩ በማብራሪያቸው፣ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ቀደም ሲል የቆሻሻ መጣያና የበሽታ ምንጭ የነበሩትን የወንዝ ዳርቻዎች ወደ ማራኪ መናፈሻዎች፣ የአረንጓዴ ስፍራዎችና የቱሪስት መስህቦች ቀይሯቸዋል። በዚህም ነዋሪዎችና እንግዶች በሰላምና በደህንነት የሚዝናኑባቸው፣ ስፖርት የሚሰሩባቸውና አዕምሮአቸውን የሚያድሱባቸው ሥፍራዎች ሆነዋል።

በተመሳሳይ የኮሪደር ልማት ስራውም፣ ሰፋፊ የእግር መንገድ አማራጮችን፣ የብስክሌት መንገዶችን፣ ዘመናዊ የመንገድ መብራቶችንና አረንጓዴ መናፈሻዎችን ያካተተ ሲሆን፤ ለከተማዋ ነዋሪዎች ምቹ፣ ለሕፃናትና ለአረጋውያን የምትስማማ፣ የትራፊክ ፍሰቷ የተሳለጠና የንግድ እንቅስቃሴዋ የደመቀ አድርጎታል። የህንጻዎች መልክና የውበት ደረጃም ከተማዋ ያላትን ዓለም አቀፍ ስም የሚመጥን እንዲሆን አስችሏል።

አዲስ አበባ ከመቆርቆሯ ጀምሮ በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። ነገር ግን ዛሬ ላይ የደረሰችበት የዕድገት ምዕራፍ፣ ከተማዋ በሕዝብ ይሁንታና ቅቡልነት ባለው መንግሥት ስትመራ ምን ያህል መሥራት እንደምትችል ማረጋገጫ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ የተመዘገበው ይህ አንጸባራቂ ድል፣ የዘመናት የልማት ቁጭትን ከመወጣት ባለፈ፣ ለቀጣዩ ትውልድ የምትመች፣ የአረንጓዴ ልማት ተምሳሌት የሆነችና በዓለም አቀፍ መድረክ በኩራት የምትጠራ ዘመናዊ መዲናን እውን አድርጓል። አዲስ አበባ ዛሬ የተስፋ፣ የውበትና የሥራ ወዳድነት ተምሳሌት ሆና ትውልዱን እያደሰች ትገኛለች።

በአንድ ከተማም ሆነ አገር ውስጥ ለሚመዘገብ ዘላቂና ፈጣን ልማት፣ የፖለቲካው ሥርዓት ባህሪ እና የመንግሥት የቅቡልነት ደረጃ ወሳኙን ሚና ይጫወታሉ። በዴሞክራሲያዊ ሂደት የመጣ መንግሥት ያለው ትልቁ አቅም የሕዝብን አቅም ያለ ምንም ማስገደድ፣ በሰላማዊና በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ መንገድ የማንቀሳቀስ ብቃት ነው። ባለፉት ሥርዓታት የነበሩ አስተዳደሮች በሕዝብ እውነተኛ ይሁንታና ምርጫ የመጡ ባለመሆናቸው፣ የሚያወጧቸው የልማት ፖሊሲዎች በነዋሪው ዘንድ በጥርጣሬና በስጋት ይታዩ ነበር። ልማት ሲባል ማፈናቀል፣ መገለል እና የጥቂቶች መጠቀሚያ መሆን ብቻ ይመስል ስለነበር ሕዝቡ የልማቱ ባለቤትና ደጋፊ መሆን አይችልም ነበር።

በሕዝብና በመንግሥት መካከል የተገነባው ጠንካራ የመተማመን ድልድይ፣ ነዋሪው በአሁኑ ወቅት እየተከናወኑ ያሉትን የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች በሙሉ ልብ እንዲቀበላቸው አድርጓል። ሕዝቡ ራሱ በመረጠውና ቅቡልነት በሰጠው መንግሥት የሚከናወኑ እነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች "ለእኔና ለከተማዬ ክብር ሲባል የመጡ ናቸው" ብሎ በጽኑ እንዲያምን አድርጎታል።

ይህ በመሆኑም ባለሀብቱ ያለምንም ስጋትና በሙሉ እምነት የራሱን ካፒታል በከተማዋ ውበትና ልማት ላይ እያፈሰሰ ይገኛል። ወጣቱ እና ሰፊው ማኅበረሰብ ጉልበቱን፣ እውቀቱንና ጊዜውን በፈቃደኝነት ለልማቱ ስኬት ሌሊትና ቀን እየገበረ ነው። ይህ ዓይነቱ መጠነ-ሰፊ የሕዝብ ንቅናቄ የሚመነጨው ደግሞ ለመንግሥት ካለው እውነተኛ ይሁንታና አክብሮት ብቻ መሆኑን ዶክተር ሙሉጌታ አስገንዝበዋል።

መንግሥት በምርጫ ወቅት የገባውን ቃልና የልማት ዕቅዶች በተግባር አሳይቶ ድጋሚ የሕዝብን አመኔታ ማግኘት ስላለበት፣ ፕሮጀክቶችን በተባለው ጊዜና ጥራት የመፈጸም ግዴታ አለበት። አሁን ለምናየው የ7/24 ሰዓት የሥራ ባህል እና ፈጣን የአፈጻጸም አቅም ዋነኛው ግፊት ይህ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ተጠያቂነት መንፈስ ነው። በልማት ሂደት ውስጥ የሚነሱ ማኅበራዊ ቅሬታዎችንና የተፈናቃዮችን ጥያቄዎች በሕግና በፍትሐዊነት ለመፍታት፣ ሰብዓዊ ክብርን በጠበቀ መልኩ ምትክ ቦታዎችንና ዘመናዊ መኖሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚደረገው ጥረት የመንግሥትን ሕዝባዊ ወገንተኝነትን ያሳያል።

አዲስ አበባ ዛሬ ያገኘችው ውበትና ልማት የድንጋይና የኮንክሪት መደራረብ ውጤት ብቻ አይደለም፤ ሕዝብና መንግሥት በዴሞክራሲያዊና በቅቡልነት መስመር ላይ ተገናኝተው የፈጠሩት የታላቅ ትብብር መግለጫ ነው። በሕዝብ ይሁንታ የመጣ መንግሥት መኖሩ ለልማቱ ሕጋዊነትን፣ ፍጥነትን፣ የሕዝብ ተሳትፎንና ዘላቂነትን በመስጠት ረገድ የማይተካ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

# ኮሌጆቹ ሰልጣኞችን ለመቀበል ምን ያህል ተዘጋጅተዋል?

**በፋንታነሽ ተፈራ**





ፎቶ-ከፋይል

ጀነራል ዊንጌት እና ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል ያደረጉት ዝግጅት በከፊል

መስከረም ተማሪዎች ከወራት እረፍት በኋላ ትምህርት የሚጀምሩበት ተናፋቂ ወር ነው፡፡ ትምህርት ቤቶችም ቅጥረ ግቢያቸውን ማስዋብን እና ግብዓት ማሟላትን ጨምሮ ለመማር ማስተማሩ የራሳቸውን ዝግጅት በማጠናቀቅ ተማሪዎችን የሚቀበሉበት ነው፡፡ የዛሬው ጽሑፋችን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት መካከል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች በ2019 የትምህርት ዘመን ሰልጣኞቻቸውን በምን አግባብ ተቀብለው ለማሰልጠን እንደተዘጋጁ እንቃኛለን፡፡

አቶ ደረሰ ጌታቸው ይባላሉ፡፡ የአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠናና አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን ናቸው፡፡ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ በ2019 የትምህርት ዘመን አዳዲስ እና ነባር ሰልጣኞችን ተቀብሎ በተሻለ ሁኔታ ለማሰልጠን ተገቢውን ዝግጅት እያደረገ ስለመሆኑ ተናግረዋል። እንደ አቶ ደረሰ ገለጻ፣ ከአዲስ አበባ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቢሮ በተሰጠው ዕቅድ መሰረት በ2019 የትምህርት ዘመን ቁጥራቸው 2 ሺህ የሚሆን አዳዲስ ሰልጣኞችን በመቀበል በመደበኛው የስልጠና መርሃ ግብር (በቀን፣ በማታ እና በቅዳሜና እሁድ) ለማሰልጠን አቅዷል። ይህ ዕቅድ ከ3 ሺህ በላይ ከሆኑት ነባር ወይም ተሻጋሪ ሰልጣኞች ጋር ተደምሮ የኮሌጁ የ2019 የትምህርት ዘመን የሰልጣኝ ቁጥር ከ5 ሺህ በላይ የሚደርስ ይሆናል፡፡

ለትምህርት ዘመኑ እነዚህን ሰልጣኞች ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝ የገለጹት ምክትል ዲኑ፤ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ በምን አይነት የትምህርት ክፍሎች (ዲፓርትመንቶች) ምን አይነት የሙያ ስልጠና እንደሚሰጥ ቴሌግራምን ጨምሮ በተለያዩ አግባቦች የማስተዋወቅ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ከፅሑፍ ማስታወቂያዎች ባለፈም መስማት የተሳናቸውንም ተደራሽ ለማድረግ የማስተዋወቅ ስራው በምስል ጭምር ተቀርፆ እንዲለቀቅ ተደርጓል፡፡ ብዙ ሰልጣኞች ወደ ኮሌጁ ስለሚመጡ ግራ መጋባት እንዳይፈጠር የቅበላ ሂደቱን የሚያስተባብሩ ሶስት ሶስት ሰዎችን የመመደብ ስራም ተሰርቷል። የስልጠና ቤተ ሙከራዎችን (ወርክሾፖችን) የማደራጀት፣ የስልጠና ግብዓት ግዢ የመፈፀምና የማስገባት ሥራ ተከናውኗል። የመቁረጫ ነጥብ ሲወጣም ባነሮችን የመለጠፍ ስራ እንደሚሰሩ አብራርተዋል።

በአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠናና አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን አቶ ደረሰ አክለው እንዳስረዱት፤ ወደ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ አዳዲስ ሰልጣኞችን በዋናነት የሚልኩት በልደታ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኙ ስምንት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ አቅራቢያ የሚገኙና ሰልጣኞች የአካባቢያቸውን ፀጋ መጠቀም እንዲችሉ የመቀስቀስና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ከትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራንና መምህራን ጋር በቅርበት እየተሠራ ነው። በቅርብ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተጨማሪ ከሰበታና ከሱሉሉታ ጭምር የሚመጡ ሰልጣኞችንም ተቀብሎ ኮሌጁ ያሰለጥናል ብለዋል፡፡

ኮሌጁ በዘጠኝ የስልጠና ዘርፎች በ23 የሙያ ዓይነቶች ከደረጃ አንድ እስከ አምስት ድረስ ነባርና አዳዲስ ሠልጣኞችን ያሰለጥናል፡፡ ከስልጠና ዘርፎቹ መካከል አውቶሞቲቭ፣ ብረታ ብረት፣ ጋርመንት እና ቴክስታይል፣ ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ፣ ቢዝነስ፣ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይሲቲ)፣ ሰርቬይንግ እና ድራፍቲንግ ይጠቀሳሉ፡፡ ስልጠናዎቹ የሚሰጡትም በዋናነት በገበያ ላይ ያላቸውን ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እውቀትንም ሙያንም የሚለግሱ ናቸው የሚሉት ምክትል ዲኑ፣ ሰልጣኞች በእነዚህ ተቋማት ሰልጥነው የራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩ ስለሚያስችላቸው ቢጠቀሙበት እንደሚያተርፉ አብራርተዋል፡፡

በተመሳሳይ በጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የህዝብ ግንኙነትና ከሙኒኬሽን ቡድን መሪ አቶ ተክሌ አስፋው ኮሌጁ ለአዲሱ የትምህርት ዘመን ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን እያደረገ ያለውን ዝግጅት በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ ኮሌጁ ከባለፈው ዓመት የተሻገሩ እና አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡ የሚቀበላቸው ሰልጣኞችም በኮሌጁ አቅራቢያ የሚገኙ የአዲስ ከተማ እና የኮልፌ ክፍለ ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና ከሸገር ከተማ የሚመጡ ናቸው፡፡

ኮሌጁ መምህራን ምን አይነት የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴን መከተል እንዳለባቸው ስልጠና ሰጥቷል፡፡ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ከክፍለ ከተማ ትምህርት ፅህፈት ቤት አመራሮች ጋር ሰልጣኞች ገበያው በሚፈልገው የሙያ ዘርፍ ሰልጥነው ውጤታማ እንዲሆኑ የግንዛቤ ፈጠራ መድረክ ተካሂዷል፡፡ ለማህበረሰቡ ቅርብ ከሆኑት ከተለያዩ የሲቪክ ማህበራት፣ የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶች ጋርም በመገናኘት እንዲሁ ሰልጣኞች በኮሌጁ በምን የስልጠና ዘርፍ መሰልጠን እንደሚችሉና ተጠቃሚነታቸው ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ ከመደበኛው የመንግስት ሚዲያዎች ጋር ውል በመፈፀም ከመስራት ባለፈ ኮሌጁ ባሉት የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች አገልግሎቶቹን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን አቶ ተክሌ ነግረውናል፡፡

ቡድን መሪው በማብራሪያቸው፣ “በትምህርት ዘመኑ ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሊገቡ የሚችሉ ተማሪዎችን ቁጥር ታሳቢ በማድረግ ኮሌጁ 2 ሺህ አዳዲስ ሰልጣኞችን እንዲቀበል ዕቅድ ወርዶለታል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በባህሪው 70 በመቶው የተግባር፣ 30 በመቶው ደግሞ የንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችንና የሰው ሃይል አሟልተን አዳዲስ ተማሪዎችን ተቀብሎ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማሰልጠን እየጠበቅን ነው። ኮሌጁ ከዕቅዱ በላይ የሆነ 5 ሺህ ሰልጣኞችን ለመቀበል የሚያስችል ዝግጅት አድርጓል” ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ኮሌጁ በስሩ 28 ሙያዎችን ባካተቱ 12 የሥልጠና ዘርፎች ሰልጣኞችን ተቀብሎ እንደሚያሰለጥን የገለጹት የህዝብ ግንኙነትና ከሙኒኬሽን ቡድን መሪው፤ ሥልጠናዎቹ በዋናነት የገበያውን ፍላጎት ታሳቢ ያደረጉ ናቸው። ኮሌጁ ከሚታወቅባቸው የስልጠና ዘርፎች መካከልም ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ፣ እንጨት ስራ፣ ብረታ ብረት፣ ሆቴል የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ በክረምቱ ወራት ወቅቱ በሚጠይቀው ደረጃ ራሱን በሠው ኃይል፣ በግብዓት፣ በቤተ ሙከራ (ወርክሾፕ) የማጠናከር እና የማደራጀት ሥራ ሠርቷል። የስልጠና ክፍሎች፣ ቤተ ሙከራዎች፣ ማሽኖች የመሳሰሉት ለሥልጠና ዝግጁ ተደርገዋል፡፡ ሰልጣኞቹ በኮሌጁ የበለጠ እንዲሳቡ ቅጥረ ግቢውን አረንጓዴ፣ ሳቢና ምቹ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቢሮ በውጤት ተኮር ስልጠናና ተቋማት ልማት ዘርፍ የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክተር አቶ ነጋ አርጋው እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደር ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሚሰጡ ስድስት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች፣ ስምንት ኮሌጆች እንዲሁም በፖሊ ቴክኒክ እና በቴክኒክ ኮሌጆች የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞችንና አመራሮችን አቅም ለመገንባት የተቋቋመ አንድ የልህቀት ማዕከል አለ፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ የመንግስትና የግል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች 34 ሺህ 200 አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል እየተዘጋጁ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ከእነዚህ ውስጥ 21 ሺህ 200 የሚሆኑት የመንግስት ኮሌጆች የሚቀበሏቸው ሲሆኑ እነዚህን ሰልጣኞች ለመቀበል ኮሌጆቹ ለስልጠና ቤተ ሙከራዎቻቸው (ወርክሾፖች) የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የማሟላት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ሰልጣኞች ወደ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብተው እንዲሰለጥኑ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ፣ በቢሮው የማህበራዊ ሚዲያ ገፆች በኦሮምኛ ቋንቋ ጭምር ማስታወቂያዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ የተበላሹ እና ጥገና የሚያስፈልጋቸው ማሽኖች በየኮሌጆቹ በተዋቀረው የጥገና ቡድን አማካኝነት በመጠገንና ለአገልግሎት በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

በ2019 የትምህርት ዘመን አዳዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል የሚደረገው ሌላኛው ዝግጅት በኮሌጆቹ አቅራቢያ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር በመገናኘት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆቹ ስለሚሰጡት ስልጠና ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና እንዲነበሯቸውም ጭምር ተደርጓል፡፡

መስከረም 26 እና 27 በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ከ100 በላይ ቀጣሪ ድርጅቶች የተሳተፉበት የስራ አወደ ርዕይ እንደተካሄደ የገለፁት አቶ ነጋ፤ ይህም የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የአዳዲስ ሰልጣኞችን የቅበላ አቅም የሚጨምር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ነጋ ገለጻ፣ አዳዲስ ሰልጣኞችን ወደ ማሰልጠኛ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች እና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የመመደቡ ተግባር የሚከናወነው በዋነኛነት ቅርበትን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች በከተማዋ ካሉ አስራ አራት የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች መካከል በአንፃራዊነት ቅርብ ወደሆኑባቸው ሄደው የሚመዘገቡ ይሆናል፡፡ ይህ ሰልጣኞች በአቅራቢያቸው ሆነው ሥልጠናቸውን እንዲወስዱ ያግዛል፤ የኮሌጆቹን የቅበላ መጠን እና የሠልጣኝ ስብጥርንም ያስጠብቃል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሰልጥነው የሚወጡ ባለሙያዎች በገበያው ላይ በጣም ተፈላጊ ናቸው፡፡ በግላቸውም ሆነ በማህበር ተደራጅተው በመሥራት ለውጤት የሚበቁበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም በሙያ፣ በክህሎት፣ በዕውቀት እና በብቃት አሰልጥነው ራስን፣ ቤተሰብን፣ ማህበረሰብን እና አገርን ለመጥቀም ወደሚያስችሉት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመግባት ከጥቅማቸው ተቋዳሽ ሁኑ ሲሉም አቶ ነጋ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## ሀገራዊ... ከገጽ 6 የዞረ

የፈጠረውን ይህን ምቹ የፖለቲካ ምኅዳር በመጠቀም፣ በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በቅንጅት በመስራት ለሕዝብና ለሀገር ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸውን ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ሠላሳ እና ከዚያ በላይ ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የነበረው ግንኙነት በስጋትና በጥርጣሬ የተሞላ፣ አንዱ ሌላውን በጠላትነት ፈርጆ የሚያሳድድበት፣ የሚያስርበትና ጥቃት የሚያደርስበት የመጠፋፋት ፖለቲካ እንደነበር በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉዓለም ኃይለማርያም ለዝግጅት ክፍላችን አብራርተዋል፡፡

መምህር ሙሉዓለም እንደ ሚያስረዱት፤ በቀደመው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ገዥውና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም መንገድ አብረው አይሰሩም። የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን የካቢኔ አባል ማድረግ ቀርቶ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ መቀመጥ እንኳን የማይታሰብበት፣ እንደ "እሳትና ጭድ" የሚተያዩበት ነበር።

በ2013 ዓ.ም ከተካሄደው 6ኛው ጠቅላላ ምርጫ በኋላ የተከናወነው የመንግሥት ምሥረታ የዚህን የፖለቲካ ባህል ውቅር የሚቀይር አዲስ ልምድ ይዞ መምጣቱን የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም ያነሳሉ፡፡ በምርጫው የሕዝብ ይሁንታ ያገኘው ገዥው ፓርቲ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች የተወጣጡ አመራሮችን በካቢኔው ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል።

በ2018 ዓ.ም ጠቅላላ ምርጫ ደግሞ ገዥው ፓርቲ ከዚህ ቀደም ይደረግ እንደነበረው የመንግሥት ሥልጣን ማጋራትን አስቀጥሏል፡፡ ይህም በፌዴራል፣ በከተማ አስተዳደሮችና በክልሎች ደረጃ በምክር ቤቶች የተለየ ድምጽና ሀሳብ እንዲሰማ እድል መፍጠሩንና የዴሞክራሲ ባህላችን እየዳበረ መምጣቱን እንደሚያመላክት የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ የሆነው ይህ አብሮ የመሥራትና ሥልጣን የማጋራት ልምድ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መምህር ሙሉዓለም ያሰምሩበታል። ሀገር የሁላችን በመሆኗ፣ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና አመራሮች ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ ለሀገርና ለሕዝብ እድገት ማዋል ይገባቸዋል። ባለፉት አምስት ዓመታትም ሥልጣን የተጋሩ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች እድሉ ሲሰጣቸው ምን ያህል ውጤታማ ሥራዎችን መሥራትና አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚችሉ በተግባር አሳይተዋል። ይህ አካሄድ ከተለያዩ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም የመጡ ሰዎች በአንድ ካቢኔ ውስጥ ተቀምጠው ውሳኔ መስጠትና አብረው መሥራት እንደሚችሉ በማስመስከር የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት ቀይሯል ይላሉ፡፡

አሸናፊው ፓርቲ ለሌሎች ሥልጣን በማጋራት አብሮ መስራት የሚቻልበት ምህዳር እየተፈጠረ ይገኛል። በመሆኑም ይህ አዲስ የፖለቲካ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ ሊሄድ እንደሚገባና ወደፊት ወደ ሥልጣን የሚመጣ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ይህን በጎ ልምድ አስቀጥሎ መሄድ እንዳለበት የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ ሙሉዓለም ያስገነዝባሉ።

የተፎካካሪ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ቢኖርባቸውም የሚያገለግሉት ሀገርና ህዝብ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ይህ አይነት ልምድ እያደገ መሄድ እንዳለበትም ተናግረዋል፡፡

በጥቅሉ መጠፋፋትን ከሚያስቀድመው የቆየ የፖለቲካ ባህል በመውጣት፣ ሥልጣንን በማጋራት በአካታችነትና በትብብር መሥራት መጀመሩ ለሀገራችን የዴሞክራሲ ዕድገት ትልቅ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ገዢው ፓርቲ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመሥራት የፈጠረው ዕድል እና የተፎካካሪ ፓርቲዎችም ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ በቅንጅት ለመሥራት ያሳዩት ቁርጠኝነት፣ ለአዲሱ የፖለቲካ ባህል መጎልበት በጎ መነሻ ይሆናል። ስለሆነም ለሀገር ዕድገት በጋራ የመቆም በጎ ልምድ ይበልጥ ተጠናክሮ ሊቀጥልና ወደፊትም ባህል ሆኖ ሊጎለብት ይገባል እንላለን።

## "የኢትዮጵያ... ከገጽ 7 የዞረ

አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ያጣችው ሕግን ባልተከተለ እና በተሳሳተ መንገድ በመሆኑ፣ መልሶ የማግኘት ፍትሐዊ መብት ያላት መሆኑን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በስፋት ማስረዳት ያስፈልጋል። በቀጣናውና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ከየሀገራቱ መንግሥታት ጋር በመወያየት፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲሁም በኢኮኖሚና ንግድ ትስስር ጥያቄው ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

በአካባቢያችን ያሉ ሀገራት ሰፊ የባሕር ጠረፍ ያላቸው ሲሆን፣ ኢትዮጵያ በተቃራኒው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ኖሯት "የመልክዓምድር እስረኛ" ሆና እንድትኖር መደረጉ ኢ ፍትሐዊ እና በዓለም አቀፍ ሕግም ተቀባይነት የሌለው መሆኑ በዲፕሎማሲያው መድረክ ሁልጊዜም እንደ ዋና አጀንዳ ሊቀርብ ይገባል። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ጉዳዩን በአዎንታዊ መልኩ እንዲረዳው የማድረግ ሥራ መሠራት አለበት። ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በመታገል በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የምትጫወተው ሚና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና አድናቆት የተቸረው እንደሆነ የሚያነሱት የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ፣ ሀገሪቱ የባሕር በር ማግኘቷም በቀጣናው ያሉ ግጭቶችን በማስወገድ፣ የባሕር ላይ ውንብድናን በመቆጣጠር ረገድ የበለጠ ሰላም፣ መረጋጋትና እድገትን የሚያመጣ እንጂ ስጋት የሚፈጥር አለመሆኑን በግልጽ ማስረዳት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ለዚህም የአፍሪካ ኅብረትና የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ-መንግሥታት ባለሥልጣንን (ኢጋድ) ማስተባበር፣ ሀገራት በጉዳዩ ላይ እምነት እንዲኖራቸው መሥራትና ጉዳዩን በጥርጣሬ ከሚያዩ አካላት ጋር የሁለትዮሽ ድርድር ማድረግ ይገባል። የኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት ታሪካዊ እውነት ያለውና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መሆኑን ለማስገንዘብ የተለያዩ የዲፕሎማሲ ስልቶችና አቅሞችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ሀገሪቱ የቀጣናውን ሰላም ለማስጠበቅ የከፈለቻቸው መስዋዕትነቶችና ውለታዎች ታሳቢ እንዲደረጉ መሥራት ይገባል። የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ታሪካዊ ሀቅና ፍትሐዊ መሠረት ያለው በመሆኑ፣ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱን በዚህ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል ለጥያቄው ዘላቂ ምላሽ ለማግኘት ያስችላል።

በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ የምርታማነት እድገት እየታየ ይገኛል። ሀገሪቱ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አጠናቅቃ ሀይል ማመንጨት የጀመረች ሲሆን፣ በቀጣይም የኒውክሊየር ሀይል ለመገንባት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች። እነዚህ ዘርፈ-ብዙ የልማት እርምጃዎች የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ ገቢ ስለሚያሳድጉት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ይታመናል።

የወጪና ገቢ ንግድ ማደግ ደግሞ በቀጣናው ከሚገኙ የጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን የወደብና የሎጂስቲክስ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምረዋል። ይህ ተፈጥሯዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል መርህ የባህር በር ለማግኘት ለምታደርገው ጥረት አቅም የሚሆንና አዲስ እድል የሚፈጥር መሆኑን የዲፕሎማሲ መምህሩ ያስረዳሉ፡፡

የባህር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማት ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥያቄው ለቀጣናው ሀገራትም ቢሆን ከኢኮኖሚና ከደህንነት አኳያ የሚያስገኘው ጥቅም የጋራ መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል። የቀጣናው ሀገራት ይህንን እውነታ በዝርዝር እንዲረዱና እንዲቀበሉ በማድረግ፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ የድርድር ማዕቀፍ በማዘጋጀት ለጥያቄው ዘላቂ ምላሽ መስጠት ይቻላል።

ማንኛውም ሀገር በራሱ ሙሉ እንዳልሆነ የሚያነሱት የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ፣ ስለሆነም ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሀገራት ከመቀበል ይልቅ መስጠትን፣ ትብብርንና አዎንታዊ የጉርብትና ግንኙነትን በማሳደግ ደጋፊ ሀገራትን ከጎኗ ማብዛት ይኖርባታል።

ከጅቡቲና ከሶማሊያ ጋር ያለውን ግንኙነት በቅርበት ማጠናከር ያስፈልጋል። ኤርትራ ከግብፅ ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለመጉዳት የምታደርገውን አሻጥር ለመቀነስና የኢትዮጵያ ወዳጆች በኤርትራ ላይ ተፅዕኖ እንዲፈጥሩ በማድረግ ቀጣናዊ ትብብሩ እንዲጠናከር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን ከኤምባሲዎችና ከቆንስላ ጽህፈት ቤቶች ባሻገር፣ በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች (ዲያስፖራው) የባህር በር ጥያቄ የትውልድ አጀንዳ መሆኑን ተረድተው በዲፕሎማሲው መስክ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስተባበር ያስፈልጋል። ይህን ትውልድ ተሻጋሪ አጀንዳ ለማሳካት በውስጥ ሀገራዊ መረጋጋትን መፍጠር ሊሰራበት እንደሚገባ የዲፕሎማሲ መምህሩ አበራ ያነሳሉ፡፡ ህዝብን፣ ምሁራንን፣ የምርምር ተቋማትንና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በማንቀሳቀስ ከመንግስት ጎን እንዲሰለፉ ማድረግ ይገባል።

የባህር በር ጥያቄ የኢትዮጵያን የነገ ሀገራዊና ቀጣናዊ ጉዞ የሚወስን ስትራቴጂካዊ አጀንዳ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ጉዳዩን በማንሳት እውነታውን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስረፅ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለጥያቄው ምላሽ ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ በመሆኑ ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

## የመዲናዋ ... ከገጽ 9 የዞረ

መኖራቸው፤ ታሪክን የሚነግሩ ሐውልቶች መገኘታቸው ለከተማዋ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ተጨማሪ አቅም ፈጥረዋል፡፡

### የኮንፈረንስ ቱሪዝምን ከፍ ባለ ደረጃ ለመጠቀም ምን ይሠራ?

አዲስ አበባን ለኮንፈረንስ ቱሪዝም የሚሆን ዕድልና ጸጋዋን በአግባቡ መጠቀም ላይ አሁንም ያልተፈቱ ችግሮች መኖራቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማማሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሃሳባቸውን ያጋሩን አቶ አሸናፊ ካሣ፤ የኮንፈረንስ ቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታየው ክፍተት እና የከተማዋን ብሎም የኢትዮጵያን እምቅ አቅም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማስተዋወቅ ውስንነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳላቸው በመጠቆም የሚመለከተው አካል ጉድለቶችን ለመፍታት ጊዜ መውሰድ እንደሌለበት አሳስበዋል፡፡

አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በጉብኝት መዳረሻዎች የአገልግሎት አሰጣጥ ጊዜ ውስንነት መኖር፣ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ የግል ባለሃብቱ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም በዘርፉ የሠለጠነ የሠው ኃይል እጥረት መኖር አዲስ አበባ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ በሚገባበት ልክ እንዳትጠቀም ተጽዕኖ ከፈጠሩባት ምክንያቶች መካከል የሚጠቀሱ ስለመሆናቸው ጠቁመዋል፡፡

አያይዘውም ችግሮችን ለመፍታት እና ከዘርፉ የተሻለ ጠቀሜታ ለማግኘት መሠራት ስለሚገባቸው ተግባራት ምክረ ሃሳባቸውን ለግሰዋል፡፡ እንደሳቸው ጥቆማ፤ የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ ዘርፉን የማስተዋወቅ ሥራ በቅንጅት መፈጸም ይገባል፡፡ አዲስ አበባ የዓየር ጠባዩንና መልክዓ-ምድሯን ጨምሮ ያላትን የቱሪዝም ሃብትና ጸጋ መለየት፣ ማልማት፣ ማስተዋወቅ እና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የኮንፈረንስ ቱሪዝም በመንግስት፣ በሚመለከታቸው ተቋማት ወይም በተወሰኑ ባለሃብቶች ጥረት ብቻ ውጤታማ ስለማይሆን፤ ህብረተሰቡ ባለቤት መሆን አለበት፡፡ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ካደረጉ ዲፕሎማቶች፣ በተለያዩ ሃገራት ካሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች፣ ከሁነት አዘጋጆች (ኤቨንት ኦርጋናይዘሮች)... ጋር በቅንጅት መሥራት ይገባልም ብለዋል፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዥ መለያ ቁጥር 01/2019 ዓ.ም

በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የመቅደላ ቅደመ አንደኛ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2019 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ ከዚህ በታች በሎት በዝርዝር የተገለፁትን እቃዎች ሎት (01)፡- የደንብ ልብስ፣ ሎት (02)፡- አላቂ የፅህፈት መሳሪያ፣ ሎት (03)፡- የህክምና እቃዎች፣ ሎት፣ (04)፡- የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ሎት (05)፡- ፈርኒቸሮች፣ ሎት (06)፡- የትምህርት ዕቃዎች፣ ሎት (07)፡- የጽዳት እቃዎች፣ ሎት (08)፡- ህትመቶች፣ ሎት (09)፡- ልዩ ልዩን እና (ሎት)10፡- ጭነትና ትራንስፖርት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው ላይ መሳተፍ የምትፈልጉ ማንኛውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እየገለፅን ጨረታውን ለመሳተፍ ተጫራቾች፡፡

1. ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባችው፡፡
2. ተጫራቾች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና በጨረታ ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወዳደሩ የተፈቀደ የምስክር ወረቀት ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡
3. ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታክስ VAT ተመዝጋቢ የሆኑና ለዚህም የተመዘገቡበትን ኮፒ አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ለሚጫረቱበት ሎት 01፣ 02፣ 03፣ 06፣ 07 እና 08 እቃዎች ናሙና ማቅረብ ግዴታ ሲሆን ሎት 04 እና 05 ት/ቤቱ በሚያቀርበው እስፔስፊኬሽን መሰረት የፎቶ ናሙና ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የት/ቤቱ ቴክኒክ ኮሚቴ በአካል መጋዘን (ወርክ ሾፕ) በመምጣት እቃዎቹን ለማየት ሲመጡ ማሳየት ይኖርቦታል፡፡ በተጨማሪም በሚቀርቡ ናሙናዎች ላይ የድርጅቱን ስም ወይም ዓርማ ሆነ ማህተም ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
5. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ሲፒዮ ለሎት 01 ብር 8000፣ ለሎት 02 ብር 4000፣ ለሎት 03 ብር 1200፣ ለሎት 04 ብር 4000፣ ለሎት 05 ብር 10000፣ ለሎት 06 ብር 6000፣ ለሎት 07 ብር 3000፣ ለሎት 08 ብር 500፣ ለሎት 09 ብር 600 እና ለሎት 10 ብር 2500 በባንክ በተረጋገጠ(CPO) ከጨረታው ሰነድ ጋር በፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይኖርባቸዋል በቼክ ማቅረብ አይቻልም፡፡
6. ተጫራቾች በወሰዱት የጨረታ ሰነድ ላይ በተዘጋጀው የዋጋ ዝርዝር መሙያ ላይ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው አማራጭ ዋጋ ግን መሙላት አይቻልም፡፡ ት/ቤቱ ካዘጋጀው የዋጋ መሙያ ሰነድ ውጭ መሙላት አይቻልም፡፡
7. ባቀረቡት ዋጋ ዝርዝር ላይ ቫት (VAT) ማካተት አለባቸው፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚጫረቱበትን የመወዳደርያ ዋጋ ሞልተው በታሸገ ፖስታ ኦርጅናል እና ኮፒ በተለያየ ፖስታ ማቅረብ ግዴታ ነው ፡፡
9. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው በተሞላው ነጠላ ዋጋ ሊሆን ይችላል ስርዝ ድልዝ ተቀባይነት የለውም፡፡
10. ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) ብር ት/ቤቱ የሒሳብ ክፍል በመክፈል መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
12. ጥቃቅንና አነስተኛ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ C.P.O እና የጨረታ ሰነድ በደብዳቤ የምናስተናግደው አምርታቹ ለገበያ በምታቀርቡት ምርት ላይ ብቻ መሆኑን እየገለፅን ጨረታው አየር ላይ የሚቆየው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ሲሆን ጨረታው በ11 ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ 4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት የሚከፈት ሲሆን ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸዉ ባይገኙም ጨረታው የሚከፈት መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ማሳሰቢያ፡- ትምህርት ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።**

**አድራሻ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የሚገኘው መቅደላ የመጀ/ደ/ት/ቤት ከፍተኛ 23 መሰናዶ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ጀርባ I.C.S አጠገብ።**

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር፡- 011-3-69-09-83/ 011-3-20-30-82 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**

**በአ.አ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ልደታ ክ/ከ ወረዳ 06 የመቅደላ ቅድመ አንደኛ አንደኛና መካ/ደ/ት/ቤት**

---

አቶ ታከለ አንጀት ቆለጭ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ መለያ ኮድ AA000100706205001002204 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለው/ይዤዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፊኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**

**ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ --- ቀበሌ --- በአዲሱ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር --- በካርታ ቁጥር 16/133/7601/00 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ፍቅርተ ወ/ብርሀን ወ/ሀና ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረቅ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡

ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልክች ትእግስት ሸዋንግዛው በቀን 20/1/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በቦሌ ሰሚት በካርታ ቁጥር ቦ/ሲሚ/149/9118/04 የሴሪ ቁጥር 021016 የቤት ቁጥር B-149/06 ወረዳ 5 የቤት ስፋት 57.30.ሜ .ካ የሆነው ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲጻፍልኝ ሲሉ አመልክተዋል። በመሆኑም ካርታው የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ማለፊያ መርሻ እንዳየን እና ይታይሽ እጅጉ ካሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ይዞታ/ቤት/ልዩ መለያ ካርታ ቁጥር /የቤቱ/የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00008110283 ሴሪ ቁጥር 0186368 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ/ይዤዋለሁ/የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን ::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ከበደ ጭኮ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ቀበሌ 16 በአሁኑ ወረዳ 03 ቤት ቁጥር ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/57/22882/00 በሴሪ ቁጥር 140758 ኦርጅናሉ ካርታ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሚሊዮን ፀጋዬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 02 የሚገኘው ይዞታ/ቤት/ልዩ መለያ ካርታ ቁጥር AA000080212792 ሴሪ ቁጥር 086617 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ/ይዤዋለሁ/የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን ::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ወ/ሮ/ወ/ሪት/አቶ/እነ አበባ መዝገቡ ወ/ሚካኤል በካርታ ቁጥር 028522 በሴሪ የካርታ ቁጥር 021830 የተመዘገበ ቤት የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

እነ ወ/ሮ ሰንገሬ ማሩፋ ሀሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000100900382 የተሰጠበት ቀን 02/11/2013 ዓ.ም በእነ ወ/ሮ ሰንገሬ ማሩፋ ሀሰን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት (አንድ ወር) ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ሰይፉ ማሞ በቀን 07/1/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በአመለከቱት በካርታ ቁጥር የካርታ ቁጥር ቦሌ 10/29/9/13/52022/00 የሴሪ ቁጥር 123942 የቤቱ ስፋት 96.7 ሜ..ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለአዲሰ ሚዲያ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ፀጋዬ ደሳለኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘው ለይዞታው የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በካርታ ቁጥር 032907 የሴሪ ቁጥር 033732 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወማ/8/6264/19 በቀን 21/1/19 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሠረት ወጪውን ግለሰቧ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የሥራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ካርታ ቁጥር ለ/ኩራ09/35/44598/0314/00 ሴሪ ቁጥር 1645292 ወ/ሮ ባየች ክብረት ይራዴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ በአቶ በየነ ሁንዴ ስም የተመዘገበ ካርታ ቁጥር 00649/1 ሴሪ ቁጥር 108131 የቦታው ስፋት 91 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ በእጃቸው ላይ ያለ ኦሪጅናል ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 30 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸዉ መሆኑን እንገልጻለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ አማኑኤል ሀይሉ ተክሌ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA00008105973 ሴሪ ቁጥር 0209920 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን ::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አብደላ ጀማል አህመድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000081200392 በሴሪ ቁጥሩ 0156952 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ------------- ቀበሌ ---------- በአዲስ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር------- በካርታ ቁጥር 16/209/10039/00 በአቶ/ወ/ሮ/እነ አረጋሽ ይህደነ መንገሻ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአመልካች አደይ አበባ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 03/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር የካርታ ቁጥር ቦሌ 10-1/107/10/2/8967/00 የሴሪ ቁጥር 1445622 ወረዳ 03 የቤቱ ስፋት 135.88 ሜ.ካ የሆነው ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲጻፍልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳወቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ /ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ንጉሴ ሺከታ የአቶ አብደላ አብደላሂ ህጋዊ ወኪል በቀን 25/01/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ቦሌ15/189/1678/00 የሴሪ ቁጥር 119858 ወረዳ 08 የቦታው ስፋት 858 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ካርታው የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳወቁን እያመለከትን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

# የዓመቱ የዓለም አትሌቲክስ ፈርጦች

- **ኢትዮጵያ በአትሌት ትዕግስት አሰፋ ተወክላለች**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት (World Athletics Athlete of the Year Award) እጅግ ታዋቂና ዓለም አቀፍ ትኩረት የሚስብ ሲሆን፣ የተቋቋመውም በኢንተርናሽናል አማተር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (አሁን World Athletics በሚባለው) አማካኝነት በእ.ኤ.አ 1988 ነበር። ይህ ዓለም አቀፍ ሽልማት በየዓመቱ በአትሌቲክስ ውድድሮች ድንቅ ብቃት ላሳዩ፣ ዓለም አቀፍ አዳዲስ ታሪኮችን ለፃፉ እና በአትሌቲክሱ ዓለም አቀፍ አርአያ መሆን ለቻሉ ምርጥ አትሌቶች የሚሰጥ የክብር ሽልማት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአትሌቲክስ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው ስኬት ተደርጎ የሚወሰደው ይህ ሽልማት፣ አትሌቶች ላመጡት ስኬት እውቅና ከመስጠቱም በላይ፣ ትውልድን የሚያነቃቁ ታላላቅ የስፖርት ከፍታዎችን የሚያከብር ዓመታዊ ታላቅ መድረክ ነው።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በዓለም አቀፍ ደረጃ በበርካታ ታላላቅ መድረኮች ላይ ከፍተኛ ስኬቶችን በማስመዝገብ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደምም በዓለም አትሌቲክስ ዓመታዊ የሽልማት ስነ-ስርዓት ላይ በርካታ አትሌቶች በእጩነት ተካትተው ውድድሩን ማሸነፋቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው።

የዓለም አትሌቲክስ ከፍታ ላይ የኢትዮጵያውያን ስም በወርቅ ቀለም ተጽፎ መኖር አዲስ ክስተት አይደለም፤ ይሁን እንጂ የትውልድ ቅብብሎሹ ሳይቋረጥ በየዘመኑ አዳዲስ ከዋክብት ብቅ እያሉ የሀገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም አደባባይ ከፍ አድርገው ሲያውለበልቡ ማየት ሁልጊዜም ልዩ ኩራት ይፈጥራል። አሁንም ያ ታሪካዊ የልህቀት ጉዞ አልተገታም።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአትሌቲክሱ ዓለም አርአያ መሆን በመቻላቸው የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት እጩ የሆኑ 10 ሴት ስፖርተኞች

በአትሌቲክስ ታሪክ ውስጥ የማይረሱ አሻራዎችን ካስቀመጡት መካከል አትሌት ቀነኒሳ በቀለ አንዱ ነው። ቀነኒሳ በቀለ በረጅም ርቀት፣ በ5 ሺህ እና በ10 ሺህ ሜትር ውድድሮች ያሳየው አስደናቂ የበላይነት እንዲሁም በአገር አቋራጭ የሩጫ ውድድር ያሳካቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው ድሎች የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማትን እንዲቀዳጅ አስችለውታል።

የአትሌት ቀነኒሳ በቀለ ድል ለኢትዮጵያ ስፖርት አፍቃሪዎች ልዩ ኩራት የፈጠረ እና ለቀጣይ ትውልድ አትሌቶች ትልቅ አርአያ ሆኖ የቆየ ነው። እንዲሁም ሌላኛዋ የኢትዮጵያ የኩራት ምንጭ የሆነችው አትሌት መሠረት ደፋር በዓለም አትሌቲክስ መድረክ ላይ ያሳየችው ድንቅ ብቃት በሽልማት ሰንጠረዡ አናት ላይ እንድትቀመጥ አድርጓታል።

መሠረት በሴቶች የ5 ሺህ ሜትር ውድድር ላይ ያስመዘገበቻቸው የዓለም ክብረወሰኖች እና በተከታታይ ዓመታት ያሳየችው ጽኑ አቋም በወቅቱ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት እጩዎች ውስጥ ተካትታ እንድታሸንፍ በር ከፍቷል።

በርካታ የኢትዮጵያ አትሌቶች የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማትን (ቀደም ሲል የአይ.ኤ.ኤፍ. የዓመቱ ምርጥ አትሌት በመባል የሚታወቀውን) ሽልማት ተቀዳጅተዋል። ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ በ1998፣ ቀነኒሳ በቀለ በ2004 እና በ2005፣ መሠረት ደፋር በ2007፣ ገንዘቤ ዲባባ በ2015፣ አልማዝ አያና በ2016፣ እንዲሁም ትዕግስት አሰፋ በ2023 ከስታዲየም ውጭ ባለው ምድብ ይህን ክብር ማግኘት ስለመቻላቸው የዓለም አትሌቲክስ መረጃዎች ያሳያሉ።

እነዚህ ታላላቅ አትሌቶች ያመጡት ድል ዛሬ ላይ እንደ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ያሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ኮከቦች የላቀ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ እና የሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው እንዲያስጠብቁ ትልቅ አቅም ሆኖአቸዋል ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ በዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ኮከብ አትሌቶች ሽልማት ውስጥ መካተቷን የዓለም አትሌቲክስ ይፋ ያደረገውም በያዝነው ሳምንት ነበር። የዓለም አትሌቲክስ (World Athletics) በየዓመቱ የሚያበረክተውና በስፖርቱ ዓለም ከፍተኛው የክብር ማዕረግ ተደርጎ የሚወሰደው የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት እጩዎች ይፋ ሆነዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት በሳበው በዚህ የሴት እጩዎች ዝርዝር ውስጥ ኢትዮጵያዊቷ የማራቶን ንግስት ትዕግስት አሰፋ በድጋሚ ስሟ ተካቷል።

ያለ አሯሯጭ የማራቶንን የዓለም ክብረወሰን ለንደን ላይ 2፡15፡41 በመሮጥ ያሻሻለችው አትሌት ትዕግስት፣ ከቀናት በፊት 52ኛውን በርሊን ማራቶን 2፡11፡04 በመግባት አሸንፋ በርቀቱ የምንጊዜም 3ኛውን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገቧ ይታወሳል። ትዕግስት በ2023 ከስታዲየም ውጪ በሚካሄዱ ውድድሮች በሚለው ምድብ ይህንኑ ሽልማት ማሸነፏ ይታወሳል።

በእርግጥ የትዕግስት አሰፋ ስኬት የጀመረው ዛሬ አይደለም። በፈረንጆቹ 2023 ከስታዲየም ውጪ በሚካሄዱ ውድድሮች ምድብ ይህንኑ የዓመቱ ኮከብነት ሽልማት ማሸነፏ የሚታወስ ነው። ያን ጊዜ ያቀናችው የልህቀት ጉዞ ዛሬም በድምቀት ቀጥሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዕጩነት እንድትቀርብ አድርጓታል።

በዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ኮከብ አትሌቶች እጩዎች ዝርዝር ውስጥ ከትዕግስት አሰፋ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዳዲስ ታሪኮችን እየጻፉ የሚገኙ ድንቅ አትሌቶች ተካትተዋል። በሴቶች ምድብ ከተመረጡት አትሌቶች መካከል ኬንያዊቷ አትሌት አግነስ ንጌቲች በረጅም ርቀት ውድድሮች ያሳየችው አስደናቂ ብቃትና ያስመዘገበችው የዓለም ክብረ ወሰን ከፍተኛ ትኩረት እንድታገኝ አስችሏታል።

አግነስ በተለይ በ10 ኪሎ ሜትር እና በአገር አቋራጭ ውድድሮች ላይ ባሳየችው ብቃት አድናቆትን አትርፋለች። እንደዚሁም አሜሪካዊቷ አትሌት ማሊሳ ጄፈርሰን እና ስዊዘርላንዳዊቷ መካከለኛ ርቀት ሯጭ አውድሪ ዌሮ በበኩላቸው ባደረጓቸው ተፎካካሪ ውድድሮች የሽልማቱን ዝርዝር ይበልጥ እንዲከብድ አድርገውታል።

የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ኮከብ አትሌቶች እጩዎች ዝርዝር ይፋ መሆን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በዓለም አደባባይ ያለውን ታሪካዊ የበላይነት እና የትውልድ ቅብብሎሽ ዳግም ያስመሰከረ ነው። ከኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ እና መሠረት ደፋር እስከ አሁኗ የማራቶን ንግሥት ትዕግስት አሰፋ ድረስ የተዘረጋው ይህ የስኬት ጉዞ፣ አትሌቶች ለስፖርቱ ያበረከቱትን ታላቅ አሻራ ያሳያል።

ትዕግስት በ2026 ውድድር ዓመት ያስመዘገበቻቸው አስደናቂ ድሎች እና ያሻሻለቻቸው የዓለም ክብረ ወሰኖች፣ በህዳር ወር በሞናኮ በሚካሄደው የክብር ስነ-ስርዓት ላይ በድጋሚ የዓመቱ ኮከብ ሆና እንድትነግስ ትልቅ ተስፋን ጥሏል።

በወንዶች ምድብ በኩል ይፋ በተደረገው የ10 እጩዎች ዝርዝር ውስጥ ሞንዶ ዱፕላንቲስ፤ አሊሰን ዶሳንቶስ እና ኬኔዝ ቤድናሬክን የመሰሉ አትሌቶች ከአስሮቹ እጩዎች ውስጥ ተካትተዋል፡፡